# ጥላ

## ዋና ስራ አስኪያጅ — General Manager

መስፍን አብርሃ — Mesfin Abraha

## ዋና አዘጋጆች — Editor In Chiefs

እየሩሳሌም ሱሞሮ — Eyerusalem Sumoro
ዳዊት ፋንታ — Dawit Fanta
ደሳለኝ አበበው — Desalegne Abebew

## አዘጋጆች — Editors

ዮሃንስ ሳምሶን — Yohanes Samson
ደበበ ከበደ — Debebe Kebede
ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል — Fisshatsion Hailegeberile

## ጽሁፍ አስተባባሪዎች — Coordinators

ብርሃኑ ባዩ — Berhanu Baue
ኤደን ዳዊት — Eden Dawit
አስናቀች ጥላሁን — Asnakch Telahun
በተወዳጅ አድነው — Betewedag Adnew
ዮሐንስ ሰላሙ — Yohannes Selamu

## የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር — Computer Graphics

ህሊና ዳዊት — Hilina Dawit


**የጥላ መጽሔት አድራሻ/Tila Magazine Address**

**Mesfin Abraha**
**An der Obergeis 1**
**36251 Bad Hersfeld**
**Email:- tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No.:- 015222195567, 017659384456, 015219261884**

# ማውጫ


ከቢን ላደን ግድያ በስተጀርባ 6

የወያኔ ግፍ ይቁም 9

ህዝባዊ መንግስት መቼ? 9

ነፃነት ማጣት ሁሉንም................! 10

ዓለም እውነት ያውራ! 10

አብዮታዊ ፕሬስ የለም ! 11

ትግላችንን እናስተሳስር 11

በዩኒቨርስቲዎች ተቃውሞው...... 11

ፓርቲያችን ይጎልብት! 12

ሰው እንደ ጎመን............. 12

የኢህአዴግ መንግስት......... 13

አፈናና ግድያ 14

አይ አለመታደል 14

ምርጫ 2007 ዓ.ም 15

ተጠያቂ ማነው? 16

ፍትህ ያጣ ህዝብ 16

በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ... 16

Democracy is ….. 18

Still no... … 18

Free Religion … 19

Blue Party 19

Arresting Journalists … 19

The neeed for democracy… 20

ስፖርት .የአውሮፓ ቻምፒየንስ ሊግ ሽፋን ገጽ …


**መልካም ንባብ**

## Where the press is free and every man able to read, all is safe.

**Thomas Jefferson**

# ABOUT TILA

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. **Tila** appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com, goolgule.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors. The articles which are posting here doesn`t represent the Magazine`s Editorial committee, rather the writers.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

## Tila Magazine is yours Magazine!


## ውድ አንባብያን

ጥላ መጽሔት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መጹሔት ነው።መጽሔቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መጽሔት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መጽሔት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መጽሔቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመጽሔቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። ጥላ መጽሔት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመጽሔቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

## ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!



# ርዕሰ አንቀጽ



## ኢትዮጵያ፡- የፕሬስ ነፃነት ሰማዕታት

የኢትዮጵያ መንግስት ሃሳብን በነፃነት የመግለፅን መብት የሚገድቡ ሕጎችን ማውጣት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ምልከታችንን እና የጉዳዩን አሳሳቢነት ስንገልጽ ቆይተናል።እነዚሁ ሕጎችንም መሰረት በማድረግ በቅርቡ ስድስት የዞን ዘጠኝ ጦማሪዎችና ሶስት ጋዜጠኞች በመንግስት ቁጥጥር ስር ውለዋል። የፌዴራሉ ፖሊስ የምርመራ ስፍራ ወደሆነው ማዕከላዊ እስር ቤትም ይገኛሉ።

እ.ኤ.አ አፕሪል 27/2014 በአራዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስረኞቹ ቢቀርቡም ትክክለኛው ክስ ምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም።ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንደሰማነው "ብሎገሮቹና ጋዜጠኞቹ  የታሰሩት ከውጭ አገር የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር በመስራት በማህበረሰብ ገፆች አማካኝነት ህዝቡን ለአመጽ በማነሳሳት አለመረጋጋት እየሰሩ ነው በሚል ነው።" ይህ ደግሞ ፀሐይ የሞቀው የፈጠራ ክስ ነው።ጋዜጠኞቹ ሌላ አገር አላቸው እንዴ?

አንዳንዶቹን ጋዜጠኖች እናውቃቸዋለን። በስነ ምግባራቸው የታነፁና የአገሪቱንም ይሁን ዓለም አቀፍ ሕጎችን አክብረው የሚሰሩ ናቸው።ታዲያ በምን ተዓምር ነው ሙያቸውን ከጋዜጠኝነት ወደ አሸባሪነት በዚህ ፍጥነት የቀየሩት?ይህ በምንም መልኩ ተቀባይነት የሌለው ነው።ከእንደዚህ አይነቱ የወረደ ተግባር ማን እንደሚጠቀም አይገባንም።


ኢህአዴግ በተረጋገጠ ህጋዊ ሁኔታ በ1997ቱ ምርጫ ከተሸነፈ በሁዋላ በርካታ ጋዜጠኞችና ብሎገሮች ታስረዋል።"በጸረ-ሽብር" ሕጉም ከ5 ዓመት እስከ እድሜ ልክ ተፈርዶባቸዋል።በተመሳሳይ "ወንጀል" በርካቶች ታስረው ፍርዳቸውን እየተጠባበቁ ናቸው።

እንደ ተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከሆነ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በሚል ጋዜጠኞችን ጦማሪዎችን የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችንና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሰራተኞችን አፍ ለማዘጋት የሚኬደው አካሄድ ተቀባይነት የለውም።ከውጭ አገር የሰብዓዊ መብት ተቋማት ጋር መስራትም በምድራችን ላይ በየትኛውም አገር ወንጀል ሆኖ አያሳስርም።አያስጠይቅምም።በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት መሰማት የጀመሩት ድምፆች በሚገርም ሁኔታ መዳፈን መጀመራቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እነዚህን በሞራልም ይሁን በሕግ ተቀባይነት የሌላቸውን "ሕጎች" በመጠቀም ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነቶችን እየገደቡ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግስት ተፈጥሯዊ የሆነ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብታቸውን ተጠቅመው የተንቀሳቀሱትንና ሌላ አላማ የሌላቸውን ጦማሪዎችና ጋዜጠኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲፈታቸው እንጠይቃለን። ጥላ መጽሔት ወቅታዊ አገር አቀፋዊና ዓለምአቀፋዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ስፖርትን አካታ ለንባብ በቅታለች።መልካም ንባብ ።**ፕሬሱን ከስቅላት ይታደጉ!**

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# EDITORIAL



## Ethiopia: Martyrs of press freedom

**We** expressed concerns about the increasing restrictions placed on freedom of opinion and expression in Ethiopia, following the recent arrest and detention of six zone 9 bloggers and three journalists. They were later taken to the Maekelawi federal police investigation station, where they remain in custody.

On 27 April 2014, they appeared before the Arada Court of First Instance in Addis Ababa. Although the exact charges against each of them remain unclear, we have received information that they were arrested for “working with foreign human rights organizations and inciting violence through social media to create instability in the country.” This is a day light fabricated accusation.

We know some of the journalists; they are very ethical and respect the national and international laws. How on earth they are changed their profession from journalism to Terrorism. This is absolutely unacceptable. We don`t know who will gonna take advantage from this rubbish and totally ignorant practices.

After EPRDF`s De jure defeat (2005), a number of journalists have been convicted under the Anti-terrorism Proclamation to sentences ranging from 5 years to life imprisonment. Two journalists arrested in July 2012 and January 2013 under the same law are currently in detention, awaiting their trial.

According to UN human right commission, ``The fight against terrorism cannot serve as an excuse to intimidate and silence journalists, bloggers, human rights activists and members of civil society organizations. And working with foreign human rights organisations cannot be considered as a crime any where in this planet. Over the past few years, the space for dissenting voices has been shrinking dramatically in Ethiopia``.

The Ethiopian authorities use these morally and legally unacceptable ``LAWS`` to restrict the rights to freedom of expression, association and assembly.

We urged the Ethiopian Government to release all bloggers and journalists currently in detention for simply exercising their right to freedom of expression. (Source- UN Human right commission) **Rescue press freedom from hanging!** As always Tila wish you a nice reading.

**TILA MAGAZINE IS YOURS MAGAZINE !**

# ከቢንላደን ግድያ በስተጀርባ

**Dawit Fanta (Engineer)/Germany**

*ልክ የዛሬ 3 ዓመት ሜይ 1, 2011፥ በዋሽንግተን ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 10:15 (ከቀትር በኋላ)።በዋይታውስ የፕሬዝደንቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተለምዶ "ሲቹዌሽን ሩም" (Situation Room) በሚባለው ክፍል ውስጥ ታዳሚዎች በታላቅ ዝምታ ተውጠው በሌላኛው የዓለም ክፍል በከፍተኛ ምስጢር እየተከናወነ ያለውን በስክሪን ይመለከታሉ።ይሁን እንጂ በሳተላይትና በድሮን (ሰው አልባ ጀት) እየታገዘ የሚተላለፈው ምስል በግቢው ውስጥ የሚከናወነውን እንጂ በቤቱ ውስጥ የሚከናወነውን ባለማሳየቱ እያንዳንዷ ደቂቃ ባለፈች ቁጥር የፕሬዝዳንቱና ከፍተኛ ሹማምንቶቻቸው ጭንቀት እያየለ መጥቷል።በዚህ መሀል ነበር በሬድዮ ድምጽ ማስተላለፊያው በኩል አንድ ድምጽ የአዳራሹን ዝምታ የሰበረው፤ እንዲህ ሲል "ጄሮናሞ! ጄሮናሞ ኤኪያ!" (Geronimo! Geronimo EKIA /Enemy Killed In Action/)።በእርግጥ ይህ መልዕክት የተላለፈው ከፓኪስታኗ አቡታባድ ከተማ ቢን ላደንን እንዲገድሉ በስውር ከተላኩት 23 ልዩ ኮማንዶዎች ከአንዱ ነበር።በወቅቱ 'ጄሮናሞ' የሚለው የኮድ ቃል ኦሳማ ቢን ላደንን የሚወክል ሲሆን የመልዕክቱም ትርጓሜ በዘመቻው ቢን ላደንን እንዳገኙትና እንደገደሉት የሚያበስር ነበር። ለመሆኑ ሲ.አይ.ኤ. ከአስር አመት እልህ አስጨራሽ ፍለጋ በኋላ ቢን ላደንን እንዴት ሊያገኘው ቻለ? 'ዘመቻ ኔፕትየን ስፒር' (Operation Neptune-Spear) በመባል የተሰየመው የ40 ደቂቃ ዘመቻስ እንደምን ተከናወነ? የሚለውን መዳሰስ የዚህ ጽሑፍ ተቀዳሚ አላማ ሲሆን ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በመስከረም 11, 2001 በኑዮርክና በዋሽንግተን ለተፈፀመው ጥቃት ከጀርባው በርግጥ አሸባሪዎች ብቻ ወይንስ የሌሎችም እጅ አለበት የሚለውን እና የአልቃይዳ መሪ የነበረውን ኦሳማ ቢን ላደንን ታሪክ በአጭሩ እንዳስሳለን።መልካም ንባብ።*

በአጠቃላይ ሲታይ በመስከረም 11, 2001 በኑዮርክና በዋሽንግተን የተፈፀመውና ከ3ሺህ በላይ ንጹሐንን የቀጠፈው አደጋ በማን ተፈጸመ? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ሶስት መልሶችን እናገኛለን።

1ኛ. በአሜሪካ መንግስት በይፋ እንደተገለፀው በኦሳማ ቢንላደንና ከፍተኛ የአልቃይዳ አመራሮች ሃሳብ አመንጪነት፣በካሊድ ሼህ መሐመድ (የአልቃይዳ የዘመቻ መምሪያ ሃላፊ የነበረ) አስተባባሪነት ቁጥራቸው 19 የሚሆኑ ወጣት የአልቃይዳ አባላት ውስብስቡን የአሜሪካ የደህንነትና የስለላ መዋቅር በማለፍ ተፈፀመ የሚል ሲሆን ይህንን ሃሳብ በዋነኝነት የሚያቀነቅኑት የአሜሪካ እና ወዳድ መንግስታት እንዲሁም በነዚህ ሀገራት የሚገኙ የሚዲያ ተቋማት ይገኙበታል።

2ኛ. ከመጀመሪያው ሃሳብ ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ በራሱ በአሜሪካ መንግስት ተፈፅሞ ውንጀላውን በአልቃይዳ አመካኝተዋል የሚል ሲሆን በዋናነት የዚህ ሃሳብ አቀንቃኞች በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ የአረብ ሃገራት ዜጎች፣ ሙስሊሞች የሚበዙባቸው የደቡብ ምስራቅ ኤዥያ ሀገራት (ፓኪስታን፣ኢንዶኔዥያ፣አፍጋኒስታን.....) እንዲሁም አንዳንድ የሴራ ንድፈ-ሃሳባውያን (Conspiracy Theorists) ይገኙበታል።

3ኛ. በዚህ ክፍል ያለው አስተሳሰብ በአብዛኛው በተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን አደጋው ሁለት አይነት መልክ አለው ብሎ ያምናል። ይኸውም በንድፍ ደረጃ (Architectural Level) እና በትግበራ ደረጃ (Working Level) ።በዚህም መሰረት ነገሩን በረቀቀ ሁኔታ በማቀድ፣ደብል ኤጀንት በሆኑ ግለሰቦች ሃሳቡን ለአልቃይዳ ከፍተኛ አመራር በማቅረብና አደጋው እንዲፈፀም መንገዶችን በመክፈት እንዲሁም በማመቻቸት በአሜሪካ መንግስት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ባለስልጣናት፣ሲ.አይ.ኤ. እንዲሁም የእስራኤሉ ሞሳድ እጅ የሚገኝበት ሲሆን ድርጊቱን በመፈፀም ደግሞ አልቃይዳ በብቸኛነት ይጠቀሳል።

በእርግጥ የሲ.አይ.ኤ. ሰዎች ራሳቸውን ቀይረው ጥሩ መካሪ መስለው ወደወጥመዳቸው ማስገባት የተለመደ አሰራራቸው እንደሆነ የሳዳም የኩዌት ወረራ ጥሩ ምሳሌ ነው።በኢራቅ-ኢራን ጦርነት ኢኮኖሚዋ ደቅቆ ከኩዌት በተበደረችው ዕዳ የምትማቅቀው ኢራቅ አይነተኛ መፍትሔ የምታገኘው ኩዌትን በመውረርና የነዳጅ ክምችት ያላቸውን ስፍራዎች በኃይል በመውሰድ እንደሆነ ፀጉረ ልውጥ የሲ.አይ.ኤ. ሰዎች ለሳዳም ሹክ ይላቸዋል።ሳዳምም ሃሳቡን ሲያወጡ ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ በዚህ ጉዳይ ላይ 'የወዳጃቸው' የአሜሪካ መንግስት አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ 'የልቤ ሰው' ያሏትን በኢራቅ የአሜሪካ አምባሳደር የነበረችውን ኤፕሪል ግላስፒን በቤተ መንግስታቸው ጠርተው ያማክሯታል።እሷም በቀጣዩ ቀን የቡሽ (አባትየው ቡሽ) መንግስት አቋም ያለችውን ነገረቻቸው፤ 'የቡሽ አስተዳደር በአረቦች መካከል በሚደረግ ጦርነት ጣልቃ አይገባም' በማለት።እግረ መንገዷን ድል እንዲቀናቸው በመመኘት ለዕረፍት በሚል ሰበብ ወደ ዲሲ በዛው ዕለት ስትሄድ ዳግም ወደ ኢራቅ እንደማትመለስ ከሳዳም ወገን ማንም አልጠረጠራትም ነበር።ሳዳምም የአሜሪካንን ይሁንታ አገኘሁ በሚል ወረራውን ሲፈጽሙ ከማንም ቀድሞ ድርጊቱን ያወገዘ ቢኖር የቡሽ አስተዳደር ሲሆን በኋላም ጦር በመስበቅ፣ዘገር በመነቅነቅ ለዘመቻውም "የበረሃው ማዕበል" (Operation Dessert Storm) የሚል ስያሜ በመስጠት ሀገራትን በማስተባበር ኢራቅን አይሆኑ ማድረግ አድርገው ቀድመው ያሰሉትን ጂኦ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በሳዳም ኪሳራ አረጋግጠዋል።

ወደ ቀደመው ነገር ስንመለስ ሲ.አይ.ኤ. እና ሞሳድ ይህን ጥቃት በንድፍ ደረጃ በማርቀቅ አልቃይዳ ፍላጎቱን እንዲያሟላ ያደረጉበት ምክንያት በዋናነት ለአሜሪካና እስራኤል ፖለቲካዊ፣ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲሆን ይህንንም የጂኦ-ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በጠንካራው የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል ለማስፈፀም የህዝብን ድጋፍና የኮንግረሱን ይሁንታ ማግኘት ግድ ስለሚል ኮንግረሱና ሴኔቱን ለማሳመንም ይሁን የአሜሪካንን ህዝብ ከመንግስታቸው ጎን ለማሰለፍ ከዚህ አይነቱ ጥቃት የተሻለ ቀስቃሽ ኃይል አይኖርም።በነገራችን ላይ ይህ አይነቱ አካሄድ በቀደሙ የአሜሪካ መንግስታትም በኩል በተደጋጋሚ የሚሰራበት ስልት ሲሆን ለምሳሌ አሜሪካ የመጀመሪያውን የአለም ጦርነት ስትቀላቀል ፕሬዝደንት ውድሮው ዊልሰን ሴኔቱንና ህዝቡን ለማሳመን የተጠቀሙት ኤስ.ኤስ.ሳሴክስ የተባለች የንግድ መርከባቸው በጀርመን ጦር ተመታ ሰመጠች በሚል የፈጠራ ታሪክ ሲሆን ከጦርነቱ በኋላ መርከቧ እንዳልሰመጠች ተረጋግጧል። በሌላ በኩል አሁንም አሜሪካ የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ዘግይታ የተቀላቀለች ሲሆን ፐርል ሀርበር የሚገኘውን የባህር ኃይል ቤዝ ለጥቃት እንዲጋለጥ

ከማድረግ ጀምሮ በቤዙ ላይ ጃፓን አደጋ ልትጥል እየተዘጋጀች መሆኑን ፕሬዝደንት ዴላኖ ሩዝቬልት መረጃው ቢደርሳቸውም አደጋው እስኪከሰት በመጠበቅ በዚያው ዕለት ሁለተኛውን የአለም ጦርነት ለመቀላቀል ምክንያት ሆኗቸዋል።

ሲ.አይ.ኤ. እና ሞሳድ ስለአደጋው መረጃ ብቻ ሳይሆን የነበራቸው አደጋው እንዲከሰትም መንገዱን እንዴት እንዳመቻቹ አደጋው ከመፈፀሙ በፊት፣አደጋው በተፈፀመ ዕለትና አደጋው ከተከሰተ በኋላ የተፈፀሙትን አስገራሚ ጉዳዮች ለማሳያነት እንመልከት።

በኦክቶበር 2000 ዓ.ም. ዩ.ኤስ.ኤስ. ኮል የተባለችው የአሜሪካ የጦር መርከብ ነዳጅ ለመሙላት በየመኗ የኤደን ወደብ በቆመችበት ጥቃት ይፈፀምባታል።ወዲያውም አልቃይዳ ኃላፊነቱን በግልጽ ይወስዳል።ሲ.አይ.ኤ. እና የየመን መንግስት በጋራ ባደረጉት ክትትል ከጥቃቱ ጀርባ የነበሩ የተወሰኑ ሰዎችን ሲይዙ በነዚህ የአልቃይዳ አባላት ላይ በተደረገ ምርመራ የዚህ ጥቃት ዋነኛ መሃንዲሶች ናዋፍ አል ሃዝሚ እና ኻሊድ አል ምህዳር እንደሆኑ ይገልፃሉ።ይህ በእንዲህ እንዳለ በጃንዋሪ 2001 ዓ.ም. አልቃይዳ በስውር በማሌዥያ ስብሰባ ያደርጋል።ይሁን እንጂ በማሌዥያ የሚገኘው የሲ.አይ.ኤ. ወኪል መረጃዎችን በማነፍነፍ እነዚህ የአልቃይዳ አባላት ከስብሰባ ሲወጡ በቅርብ ርቀት ፎቶ ያነሳቸዋል።በዚህም መሰረት በሲ.አይ.ኤ. ጥቁር መዝገብ ላይ የሚገኙትና በጥብቅ የሚፈለጉት ናዋፍ አል ሀዝሚ እና ኻሊድ አል ምህዳር በዚህ ስብሰባ እንደተሳተፉ ይረጋገጣል።ከዚህም ባሻገር በነዚህ ሁለት ሰዎች ላይ ክትትል ሲደረግ በአስገራሚ ሁኔታ ከ10 ቀናት በኋላ በጃንዋሪ 15, 2001 ዓ.ም. የበረራ ትምህርት ለመማር ወደ ሎሳንጀለስ ይጓዛሉ። ይህም መረጃ ቁጥራቸው ቢያንስ ከ60 በማያንስ የሲ.አይ.ኤ. ቁልፍ ሰዎች ይታወቅ ነበር።እናም ከሰባት ወራት በኋላ አውሮፕላን ከጠለፉት 19 ወጣቶች መካከል እነዚህ ሁለቱ ይገኙበታል።ለመሆኑ በጥቁር መዝገቡ ላይ ካሰፈራቸው ዘንድ በሲ.አይ.ኤ. አፍንጫ ስር ያውም በሎሳንጀለስ ያለምንም እንከን ለሰባት ወር ሲቆዩ ቁልፍ የሲ.አይ.ኤ ሰዎች ለምን ዝምታን መረጡ?FBI በነዚህ ግለሰቦች ላይ በሌሉበት ክስ መስርቶ እየፈለጋቸው ሳለ ሲ.አይ.ኤ. ይህን ወሳኝ መረጃ ሆን ብሎ ከ FBI መደበቅ ለምን ፈለገ? እርግጥ ነው ሲ.አይ.ኤ. አስቀድሞ በነደፈው ውስብስብ ወጥመድ በመግባት የቤት ስራውን እየሰሩለት ስለነበር ብቻ ነው።

በሌላ በኩል የአሜሪካ መንግስት አይቶ እንዳላየ ሆኖ ያለፈው የሚከተለውን ይመስላል።በምህፃረ ቃል "ኖራድ " (North America Aero-Space Defence Command) በመባል የሚጠራው ግዙፍ መንግስታዊ ተቋም በሳተላይትና በሬዳር በመታገዝ የአሜሪካንን አየር ክልል ከጥቃት ይከላከላል።ከዚህ ጎን ለጎን አውሮፕላኖች በአሜሪካ ግዛት ሲጠለፉ የፌደራል ኤቬሽን አድሚንስትሬትሬሽን መስሪያ ቤት ወዲያው ለኖራድ ሲያሳውቅ ኖራድም ሃያ አራት ሰዓት በተጠንቀቅ የሚጠብቁ እጅግ ፈጣን የጦር ጀቶችን በማስነሳትና የተጠለፈውን አውሮፕላን በመከበብ በተለይ የተጠለፈው አውሮፕላን የበረራ መስመሩን ከቀየረና መሬት ላይ ካለው የበረራ መስመር ተቆጣጣሪ ጋር ግንኙነቱን ካቋረጠ ተገዶ እንዲያርፍ የሚደረግ ሲሆን ለማረፍ ፈቃደኛ ባይሆን የጦር ጀት አብራሪው ያለምንም ተጨማሪ ትዕዛዝ የተጠለፈውን አውሮፕላን መትቶ ይጥለዋል።ይህም ቢበዛ ከ5-10 ደቂቃ የሚፈጅ ጉዳይ ነው።በመሆኑም በመስከረም 11, 2001 የመጀመሪያው አውሮፕላን እንደተጠለፈ እና ከበረራ መስመር በመውጣት የግንኙነት መስመሩን ሲያቋርጥ የአቬሽን መስሪያ ቤት ለኖራድ ያሳውቃል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሁለተኛ አውሮፕላን እንደተጠለፈ እና ከበረራ መስመር በመውጣት የግንኙነት መስመሩን እንዳቋረጠ ለኖራድ ይገለጽለታል።ይሁን እንጂ በኖራድ በኩል ምንም እንቅስቃሴ የለም።እንዲሁ ሶስተኛው አውሮፕላን ከተጠለፈ ከ 30 ደቂቃ በላይ በሮ ፔንታጎንን ይመታል። ይህም ማለት የመጀመሪያው አውሮፕላን ከተጠለፈ ከ109 /መቶ ዘጠኝ/ ደቂቃ በኋላ ኖራድም አውቆ ካንቀላፋበት ከባድ "እንቅልፍ " ነቅቶ በባዶው ሰማይ ላይ እነዚያን እጅግ ዘመናዊና ፈጣን ጀቶች ሲያስጓራቸው ዋለ።እዚህ ጋር ለንፅፅር ይረዳ ዘንድ አንድ እውነተኛ ታሪክን እናንሳ። በኦገስት 28, 2010 ዓ.ም. ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሆነ የመንገደኞች አውሮፕላን ወደ እስራኤል ይጓዛል።ይሁን እንጂ የእስራኤል አየር ክልል ሊገባ ሲል የኮሚኒኬሽን ኔትዎርክ ችግር በድንገት ይፈጠራል።በመሆኑም የአውሮፕላኑ አብራሪ ከእስራኤሉ የበረራ መስመር ተቆጣጣሪ ጋር መገናኘት ባለመቻሉ ይህ የኤቬሽን ሰራተኛ ለእስራኤል አየር ኃይል ያሳውቃል። በአስገራሚ ፍጥነት አውሮፕላኑ ገና የእስራኤል የአየር ክልል መዳረሻ እያለ ነበር በሁለት የጦር ጀቶች የተከበበው።እናም ቤንጎሪዮን ኢንተርናሽናል ኤርፖርት ማረፍ የነበረበት የኛው አውሮፕላን ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ በእስራኤል የአየር ኃይል ቤዝ ተገዶ ማረፍ ችሏል።

እንግዲህ የአሜሪካኑ ኖራድ ከእስራኤል አየር ኃይል አንፃር ሲለካ በሁሉም መስፈርት ከንፅፅርም በላይ እጅግ የተሻለ ሲሆን ለመቶ ዘጠኝ ደቂቃዎች አንዲት ጀት ማስነሳት ለምን እንዳቃተው እውነተኛው ምላሽ በእጃቸው ካለ ሰዎች መካከል በዕለቱ የመከላከያ ሚንስትር ማዕረጉንና ኃላፊነቱን ረስቶት ይሁን ትቶት በፔንታገን የቆሰሉ ሰዎችን በቃሬዛ ወደ አምቡላንስ ሲያመላልስ የታየው ዶናልድ ራምስፊልድ አንዱ ነው።

የአሜሪካ መንግስት በጉዳዩ ላይ እጁ እንዳለበት በርግጥ ከጥርጣሬ በላይ የሚያደርጉን በርካታ ማሳያዎች ቢኖሩም ይህን ለጊዜው በዚህ እንግታውና ወደ ሞሳድ እና እስራኤል እንሂድ።

የመጀመሪያው አውሮፕላን ከመንታዎቹ ህንፃ አንዱን ሲመታ በኑዮርክና አካባቢዋ የሚገኙ ነዋሪዎች በታላቅ ድንጋጤ ተውጠው በቅርብ ያሉት አንጋጠው በርቀት ያሉትም አቅርቦ በሚያሳይ መነፅር (Binocular) ከቤታቸው ሆነው በእሳት ታፍነው መውጫ ያጡትንና አንዳንዴም ከዚያ ሰማይ ጠቀስ ህንፃ ላይ የሚዘሉትን ሰዎች እያዩ በሀዘን ተውጠዋል።ማሪያ የተባለችውም ወይዘሮ ይህን ትዕይንት በሀዘን ተውጣ በመነፅሯ (Binocular) ከሂዩድሰን ወንዝ ማዶ ከሚገኘው ቤቷ ትመለከት ነበር።ነገር ግን በዚህ መሀል ከቤቷ በቅርብ ርቀት በሚገኝ አንድ ቤት ጣሪያ ላይ ቁጥራቸው አምስት የሚደርስ ወጣቶች እየተቃቀፉ፣እየጨፈሩ፣ የሲጋራ ላይተራቸውን እንደሻማ እያበሩ፣ወደሚነደው ህንፃ እየተጠቋቆሙ ፊልምም እየቀረፁ ነበር።በሁኔታው እንግዳነት ግራ የተጋባችው ማሪያ ለFBI ለመደወል ጊዜ አልወሰደባትም።በስኮት ዲ ካርሎ የተመራው የFBI ቡድን በቦታው ደርሶ እነዚህን ሰዎች በቁጥጥር ስር ያውላል። ከነዚህም መካከል ወንድማማቾቹ ሲቪያን ኩርዝበርግ እና ፖል ኩርዝበርግ እንዲሁም ኦዴድ ኤልነር፣አሜር ማርማሪ እና ያሮን ሽሙኤል ሲሆን አምስቱም እስራኤላውያን ከመሆናቸውም ባሻገር ወንድማማቾቹ ሲቪያንና ፖል መደበኛ የሞሳድ አባል ነበሩ።በግቢው ውስጥ ከተያዘችው መኪናቸው ውስጥ በስማቸው የተዘጋጁ የበርካታ ሀገራት ፓስፖርት፣4,700 ዶላር በካሽ በሲቪያን ካልሲ ውስጥ ሲገኝ በምርመራም መኪናቸው የሚፈነዱ ኬሚካሎች ጭና እንደነበር ይደረስበታል።ነገር ግን ለ71 ቀናት ብቻ በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ከተደረገ በኋላ "የቪዛ ህግ በመተላለፍ" (visa violation) በሚል ወደ እስራኤል እንዲመለሱ የተደረገ ሲሆን የአምስቱን እስራኤላውያን የክስ ሂደት በማቋረጥና ጉዳዩን ከ FBI እጅ በማውጣት የፍትህ መስሪያ ቤቱን በበላይነት ይመራ የነበረው አይሁዳዊው አተርኒ ጄነራል (Attorney General) ማይክል ክርቾፍ ሚና ከፍ ያለ ነበር። ይህም FBI ከዚህ ጉዳይ ሆን ተብሎ እንዲገለል ለመደረጉ ሁለተኛ ማሳያ ነው።

በርግጥ ሁለቱም ህንፃዎች ባለቤትነታቸው የአይሁዳዊው ቢሊየነር ሌሪ ሲልቨርሽታይን (ከኢንሹራንስ ክፍያ በርካታ ገንዘብ በማግኘቱ ከጥቃቱ ትርፍ ካጋበሱት ግለሰቦች አንዱ ነው) ሲሆኑ እነዚህ ህንፃዎች ከመውደቃቸው ቀደም ብሎ ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምፅ የነበር ሲሆን ምናልባትም ሲፐርተርማይት በመባል የሚታወቀውንና ህንፃዎችን ለማፍረስ የሚጠቀመውን ተቀጣጣይ ኬሚካል በህንፃው ቋሚዎች ላይ በማድረግና ተሸካሚ ብረቶቹን በከፍተኛ ሙቀት እንዲቀልጡ በማድረግ ህንፃዎቹ በራሳቸው ክብደት እንዲፈርሱ ሳይደረግ አልቀረም።ለዚህም ይመስላል የአሜሪካ መንግስት ከአደጋው ጥቂት ወራት በኋላ መረጃን ለማጥፋት በሚመስል መልኩ የህንፃውን ብረቶች (Structural Steel) ወደ ቻይና ኤክስፖርት ያደረገው።ለግንዘቤ ይረዳ ዘንድ በእለቱ የፈረሱት ህንፃዎች በስፋት እንደሚነገረው ሁለት ሳይሆኑ ሶስት ናቸው። የሶስተኛው ህንፃ መውደቅ በስፋት በታላላቅ ሚዲያዎች ያለመወራቱ አንድም በአስገራሚ ክስተቶች የተሞላ ስለነበር ነው። በተለምዶ ህንፃ ቁጥር-7 (Building-7) በመባል የሚታወቀው ባለ 47 ፎቅ ህንፃ ንብረትነቱ የዛው አይሁዳዊ ሌሪ ሲልቨርሽታይን ሲሆን በዕለቱ እንደሁለቱ ህንፃዎች በአውሮፕላን ካለመመታቱም ባሻገር ከሁለቱ ህንፃዎች መፍረስ በኋላ ለሰባት (7) ሰዓታት ያህል ያለችግር ቆሟል።ይሁን እንጂ የቢቢሲ ዘጋቢ ማን እንደላካት እስከዛሬ እንቆቅልሽ ቢሆንም ህንፃው ከመውደቁ 20 ደቂቃ ቀድማ ያውም ህንፃው ፊትለፊት በቅርብ ርቀት ቆማ በቀጥታ ስርጭት ለዘጠኝ ደቂቃዎች ያህል "ህንፃ ቁጥር-7 ከጀርባዬ እንደምትመለከቱም ወድቋል" እያለች መዘገብ ትጀምራለች፣ይሁን እንጂ ጋሪው ከፈረሱ የቀደመባቸው የዚህ ጉዳይ አርኪቴክቶች ከረፈደ በኋላ የቀጥታ ስርጭቱን ያቋርጡታል።ከሃያ ደቂቃ በኋላም ህንፃው በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ በሥነ-ህንፃ ትምህርት "ኮንትሮልድ ዲሞሊሽን" በሚባለው አይነት ሁኔታ ወድቋል።ለዚህም ተመሳሳይ ሱፐርተርማይት የሚባለውን ኬሚካል ሳይጠቀሙ እንዳልቀረ የሚገመት ሲሆን ተከታታይ የፍንዳታ ድምጽ ከህንፃው መውደቅ ትንሽ ቀደም ብሎ ይሰማ ነበር።



በሌላ በኩል ይህ ጉዳይ ከሞሳድና እስራኤል ጋር እንዲያያዝ የሚያደርገው ጥቃቱ በተፈፀመበት ዕለትና ሰዓት ቢያንስ ቁጥራቸው ወደ አራት ሺህ የሚገመት አይሁዶች በዚህ ህንፃ ለመደበኛ ስራ መገኘት ሲኖርባቸው በዕለቱ የሞተው አንድ አይሁዳዊ ብቻ ነው።ይህ በአጋጣሚ ወይ በተአምር የተፈፀመ አይደለም።ነገሩ እንዲህ ነው፡- ጥቃቱ ከመፈፀሙ ሁለት ሰዓታት ቀደም ብሎ "ኦዲን ኢንስታንት ሜሴጅ ኢንክ." ተብሎ የሚጠራው አጭር የፅሁፍ መልዕክቶችን የሚያስተላልፈውና ንብረትነቱ የእስራኤል የሆነው (ይህ ድርጅት በአሜሪካ ኑዮርክና በእስራኤል ሄርዝልያ ከተሞች ቢሮዎች ያሉት ሲሆን በተለይ በሄርዝልያ ከሚገኘው የሞሳድ ኦፊሻል ቢሮ ጋር ግንኙነት እንደነበረው በሰፊው ይነገራል) ድርጅት ለአይሁዳውያኑ በአካባቢው ላይ ጥቃት ሊፈፀም ስለሆነ ስፍራውን ለቀው እንዲሄዱ ያሳሰባቸዋል።በመሆኑም መልዕክቱን ለFBI ወይም ለሌላ አካል ሳይናገሩ ራሳቸውን ብቻ ማትረፍ ችለዋል።ከአደጋው በኋላ ይህ ጉዳይ ይፋ ሲወጣ የኦዲን የስራ ኃላፊ ተጠይቀው ለጋዜጠኞች መልስ ሲሰጡ "ከሄርዝልያ እስራኤል ከሚገኘው ቢሯችን ሁለት ሰራተኞች መረጃውን ከየት እንዳመጡት ባናውቅም እነሱ ናቸው ያስተላለፉት" በማለት ነገሩን የሁለት ሰራተኞች ጉዳይ ለማስመሰል ቢጥሩም በኦዲን አፍንጫ ስር ያለው ሞሳድ ዜጎቹን ለመታደግ የወሰደው አማራጭ መንገድ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል። በእርግጥ የጥቃቱስ አላማ የአሜሪካንን ህዝብ በቁጣ አነሳስቶ ከመንግስታቸው ጎን እንዲሰለፉ በማድረግ ቀድሞ ወደ ታቀደ ጦርነት መግባት እንጂ እስራኤሎችን ለመግደልማ ሃማስና ሄዝባላህ መቼ አነሱ?

ሌላው እስራኤልን ከዚህ ጥቃት ጋር የሚያገናኝ እና ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ቢኖር በምህፃረ ቃል አይ.ሲ.ቲ.ኤስ. ኢንተርናሽናል በመባል የሚታወቀውና የኤርፖርት ደህንነትን በመጠበቅ አገልግሎት ላይ የተሰማራውን የእስራኤል ድርጅት ጉዳይ ነው።አይ.ሲ.ቲ.ኤስ. ኢንተርናሽናል ዕዝራ ሐሬል እና ሜናኬም ኤዝመን በሚባሉ እስራኤላውያን ባለቤትነት የሚተዳደር ሲሆን በአለማቀፍ ደረጃ እጅግ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም በተለያዩ ሀገራት ለሚገኙ ኤርፖርቶች የፍተሻና ደህንነት አገልግሎት ይሰጣል።ይህን ድርጅት ውጤታማ እና ዝነኛ እንዲሆን ካስቻሉት ጉዳዩች መካከል በደህንነቱ ዙሪያ የሚሰሩ ሰራተኞቹ በአንድ ወቅት "ሺን ቤት" (Shin Bet) በመባል በሚታወቀው የእስራኤል የሀገር ውስጥ ደህንነት (የእስራኤል የደህንነት መዋቅር በሶስት የተከፈለ ሲሆን ወታደራዊው የደህንነት መስሪያቤት "አማን" የሚባል ሲሆን የሀገር ውስት ደህንነት መስሪያ ቤቱ "ሺን ቤት" ይባላል እንዲሁም የውጭ ደህንነቱ ደግሞ "ሞሳድ" ይባላል።) ሠራተኞች የነበሩ በመሆናቸው ነው።እናም በመስከረም 11, 2001 ዓ.ም. የተጠለፉት አውሮፕላኖች የተነሱባቸው ሶስቱም ኤርፖርቶች ማለትም ዳለስ፣ለገን እና ኒዋርክ ኤርፖርቶች በአይ.ሲ.ቲ.ኤስ. ኢንተርናሽናል ጥበቃ ስር የነበሩ ሲሆን ጠላፊዎቹ ለበረራ ደህንነት እጅግ አደገኛ የሆኑ ስለቶችን፣አንድ ሽጉጥ እና መሰል ነገሮችን እንዴት በቀላሉ ይዘው ገቡ?በዕለቱስ ኤርፖርት የነበሩ የቅኝት ቪዲዮዎች (Surveillance Videos) እንዴት "ጠፉ" ተባለ?

በንድፍ ደረጃ (Architectural Level) ስለሚገኙት አካላት ይህንን ያህል ካልን በትግበራ ደረጃ (Working Level) የነበረውን አልቃይዳን ከምስረታው 1993 ጀምሮ በበላይነት ሲመራ የነበረውን ኦሳማ ቢንላደንን ታሪክ ባጭሩ እንመልከት።

የኦሳማ ቢንላደን እናትም ሆኑ አባት በትውልድም ይሁን በደም ሳዑድ አረባዊያን አይደሉም።አባቱ መሐመድ ቢን አዋድ ቢን ላደን ትውልዱም ይሁን ዕድገቱ ከየመኗ ሃድራሞት ይጀምራል።የሃድራሞት አካባቢ ሰዎች በስነ ህንፃ ችሎታቸው የተካኑ ሲሆን መሐመድም ከሃይማኖታዊ ትምህርት የዘለለ የዘመናዊ ትምህርት ዕውቀት ባይኖረውም ከፍተኛ የማስታወስ ችሎታ የነበረውና የተዋጣለት የህንፃ ባለሙያም ነበር።ይሁን እንጂ በ22 ዓመቱ ማለትም እ.ኤ.አ. በ1930 ዓ.ም. በየመን በተለይም በሃድራሞት በተከሰተው ከፍተኛ ድርቅና ረሃብ በርካታ የሃድራሞት ወጣቶች ነፍሳቸውን ለማትረፍ ሲሰደዱ መሐመድም ከነዚህ አንዱ ነበር። የኦሳማ ቢንላደን አባት መሐመድ ቢን አዋድ ለመጀመሪያ ጊዜም ስደትን የጀመረው በእኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ነበር።**ዋቢ መፃሕፍት** (**Reference books**):-1. The Looming Towers, by Lawrence Wright. 2. No Easy Day, by Mark Owen. 3. Man Hunt, by Peter L. Bergen. 4. Solving 9/11, by Christopher Bollyn. **(ተከታዩ ክፍል በቀጣዩ እትማችን ይቀጥላል)**

# የወያኔ ግፍ ይቁም!

**Selamawet Tamerat/ Langenselbold**

ዛሬ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከድጡ ወደ ማጡ እያመራች ነው። አምባገነኑ መንግስት ወደብ አልባ ያደረጋት ሳይበቃው ለዘመናት ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ያደረጋትን ወታደሮቿን በትኖ ለድህነት ለረሃብ መዳረጉ ሳያንሰው ጥንት ጀምሮ በቅርስነት የኖረ ወርቅ አልማዝ የከበሩ ማዕድኖቿን ወዳልታወቀ ቦታ በማጓዝ ዙሪያዋን እንደ ዳቦ እየቆራረሰ ለጎረቤት አገር ሲያድላት ኖሯል።አረመኔውና አምባገነኑ መንግስት ተዋዶ የኖረውን ህዝብ በዘር በሃይማኖት ከፋፍሎ ሲያፋጀው ይስተዋላል።በአማራ በአኝዋክ በሶማሌ በሲዳማ በኦሮሚያና በመሳሰሉት አካባቢዎች በዚሁ ከፋፋይ አገዛዙ የዘር ማጥፋት ወንጀል በማካሄድ ላይም ይገኛል።በኢንቬስትመንት ሰበብም ነዋሪዎችን በተለይ ህፃናት ለጎዳና ተዳዳሪነት አዋቂዎች ለልመና እንዲዳረጉ አስገድዷቸዋል።

አሁንም ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በከፍተኛ እንግልትና የግፍ ጭፍጨፋ ላይ ይገኛሉ።አገሪቱን በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የጣለው ሳይበቃው በሙስሊሙ ህብረተሰብ እምነት ጣልቃ ገብቶ የእርስ በርስ ፍጅት እየፈጠረ ነው። የወያኔ መንግስት በተመሳሳይ ሁኔታ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥም ጣልቃ በመግባት አድባራትና ገዳማትን እያፈረሰ እያቃጠለ ታቦታትና ንዋየ ቅዱሳትን እያዘረፈ ይገኛል።

ስርዓቱ በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በጋዜጠኞችና በሌሎች ምሁራን ላይ ኢሰብዓዊ ግፍ እየፈፀመ ይገኛል።በዚህም የተነሳ አብዝሃው ሕዝብ ለስደትና ለእስር ተዳርጓል። ይህ አምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የሚፈፅመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰትና አድልዎ እንዲያቆም የተባበሩት መንግስታት የአውሮፓ ህብረት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ለጋሽ ድርጅቶች እርምጃ ሊወስዱበት ይገባል።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# ወያኔ፡- የነገው ትውልድ እንቅፋት

**Ybekal Engeda/ Kassel**

ስለ ዴሞክራሲ ብዙ ሲነግረን የኖረው የኢህአዴግ መንግስት ጭራሽ ዴሞክራሲው አፈና ድብደባና ግድያ ከሆነ ውሎ አድሯል።የህዝቡ የዴሞክራሲና የነፃነት ጥያቄ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅትም የወያኔ መንግስት ምንም አይነት የአመለካከት ለውጥ ሳያሳይ አፈናውን አጠናክሮ ቀጥሎበታል።

አሁን አሁን ለይምሰል የሚፈቀዱት ሰላማዊ ሰልፎች በተለያዩ የማደናቀፊያ ዘዴዎች ታጅበው ቢካሄዱም የተፈለገውን ውጤት አላመጡም ግን ለወደፊቱ ሰላማዊ ሰልፎቹን ወደ ህዝባዊ ማዕበልነት ለመለወጥ ጥሩ ዘዴዎች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።ጎን ለጎን ግን የወያኔ መንግስት ሃይማኖትን ከሃይማኖት ብሄርን ከብሄር ጋር በማጋጨት የህዝቡን አንድነት የመበታተን ስራ እየሰራ ይገኛል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የአዲስ አበባን አዲስ ማስተር ፕላን መነሻ በማድረግ ተቃውሞ ባሰሙ የኦሮሚያ ክልል የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በመቀጥቀጥ በማፈንና በመግደል የዴሞክራሲ መብቶችን መድፈቁን ወያኔ ተያይዞታል።እስካሁንም እስከ 60 የሚደርሱ ወጣቶች መገደላቸውና የደረሱበት መጥፋቱን የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በመዘገብ ላይ ናቸው።

በደሉንና ግፉን የምንሸከምበት አቅማችን አሁንስ እየተሟጠጠ ነው።ስለዚህ ወገኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ትውልድን ለማጥፋት በመስራት ላይ ያለውን ይህንን አገዛዝ ለማስወገድ አንድ እንሁን እልሃለሁ።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# ህዝባዊ መንግስት - መቼ?

**Rahel Worknhe Tessma/ Gemünden**

አያሌ ኢትዮጵያውያን (ዜጎች) ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት በሚል ለዘመናት ደምና አጥንታቸውን ከስክሰዋል።ነገር ግን በየጊዜው ይህንኑ ህዝባዊ ትግል በማስቀየስ ለግል ጥቅማቸው የቆሙ መንግስታት የመንግስት ስልጣኑን ተቆናጠው ለስልጣኑ መሰረት የሆናቸውን ህዝብ ሲያቆረቁዙት ኖረዋል በማቆርቆዝ ላይም ናቸው።

ሁሉም ወደ ስልጣን ሲመጣ ለህዝቡ የሚገባውን ቃል ወደ ጎን በመተው ስልጣኑን ለማራዘም የሚያመቹትን የአፈና መዋቅሮች እየዘረጋ እልፎች የተሰውለትን ህዝባዊ መንግስት ከማቋቋም ቦዝኖ ከህዝቡ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ አወዳደቁ የባቢሎን እየሆነ ነው።

ህዝቡን እኛ እናውቅልሃለን የሚሉት ስርዓታትም መጨረሻቸው ምን እንደሆነ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የሌላ አገር ምስክርነት አያሻንም።አሁን ያለው የወያኔ መንግስትም በስመ ምርጫ ለዘላለም ሊገዛን አልሞ በመከራና በእንግልት ውስጥ ከከተተን ውሎ አድሯል።

ስለሆነም በስመ ምርጫና ዴሞክራሲ የግፍ አገዛዙን የጣለብንን አምባገነኑን የወያኔ/ ኢህአዴግ ስርዓት ለማስወገድ የተሞከሩት ሰላማዊ መፍትሄዎች ሁላ ባለመስራታቸው በአነስተኛ ኪሳራ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ የግድ የሚልበት ሰዓት ላይ ስለደረስን ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ እውነተኛውን ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት ቀጠሮ መያዝ የለብንም።ዛሬ ወስነን እንነሳ!

# ዘመቻ ማፍረስን እንግታ!!!

**Betewedag Adnew/Bayreuth**

በዋልድባ ገዳም እየተካሄደ ያለው እምነትን የማፍረስ ዘመቻ ዛሬም እንደቀጠለ በቦታው የሚገኙ መነኮሳት በምሬት እየገለፁ ነው፡፡ ቀደም ሲል ወደ 20 የሚጠጉ ገዳማትን ለማፍረስ ተንቀሳቅሶ የነበረው የኢህአዴግ አፍራሽ ሀይል በመነኮሳት ፣ በባህታውያን፣... ፀሎትና በአካባቢው በሚገኙ ተቆርቋሪዎች ሲከሽፍበት የዘጉ ባህታውያንና ጨምሮ በርካቶችን በማሰር ፣ በመደብደብ፣በማፈናቀልና በማንገላታት ጉዳት ማድረሱ ይታወቃል፡፡ በዚህም ያተረፈው 2ቱን ‹መሪዎችን› መለስ ዜናዊና አቡነ ጳውሎስ ፣ በቦታው የሄዱ መሀንዲስና ሰራተኞችን፣ ጠበንጃ አንጋቾችን ጨምሮ በርካቶችን በሞት ሲነጠቅ በራሱ ላይ ከፍተኛ ችግር አድርሷል፡፡

ይሁንና በየጊዜው ኪሳራን እየተከናነበ በሀገርና በሕዝብ ላይ በደል የሚያደርሰው ኢህአዴግ በ16/ 08/ 2006 ዓ. ም በዕለተ ሀሙስ ማይ ለበጣ በተባለ ቦታ የገዳማትን ሰዎች ሰብስቦ ፡- 1ኛ፡- ድልስ ቆቃ አቡነ- አረጋዊ ገዳም፣ 2ኛ፡- መሀር ገፅ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም፣ 3ኛ፡- እጣኖ ማርያም ገዳም ፣....‹ለስኳር ልማት› እንዲፈርሱ በቀጣይ ደግሞ ማይጋባ ቅ/ ጊዮርጊስ ‹ ይነሳሉ› የሚል ሀሳብ ሲያቀርብ በርካታ ተቃውሞ ተነስቶ ከፍተኛ ውዝግብ ፈጥሯል፡፡ በመሀል የሰገሰጋቸው ደጋፊዎቹ የድጋፍ ድምፅ ሲያሰሙ መነኮሳትና መናንያን ተቃውሞሙን በማጠናከራቸው ለድጋሚ ውይይት ለግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ. ም ተቀጥሯል፡፡ በዚህም የዋልድባ ገዳም ተቆርቋሪ የሆንን ሁሉ ድምፃችንን ከፍ አድርገን ልናሰማ ይገባል፡፡

# ነፃነት ማጣት ሁሉንም ማጣት !

**Tigist Birko Tafa/Bad soden Salmünster**

በወያኔ የሃያ ሁለት አመታት አገዛዝ በቀጠለው የጅምላ እስርና እንግልት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሰዶ ማሳደዱ ቀጥሎ በሺዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎቻችን ማዕከላዊ ተብሎ በሚታወቀው የምርመራና የስቃይ ስፍራ አሳራቸውን እያዩ ነው።

ህዝባችን በአስተሳሰብ ልዩነቱ ብቻ የአንድ ሀገር ዴሞክራሲያዊነት መለኪዎች ከሆኑት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ውጪ ለእስርና ለእንግልት እንደሚዳረግ የአደባባይ ምስጢር ነው።ወያኔ በተደጋጋሚ በዘመቻ መልክ ባልተረጋገጡ ወይም ሊረጋገጡ በማይችሉ አሉባልታዎች በርካቶችን ከማሠሩም በላይ ሞት እየፈረደባቸው ይገኛል።ሥርዓቱ መገልገያ መሣሪያ እያደረገ ያለው የፀረ-ሽብር ህግ ተብሎ የሚታወቀውን የህግ ረቂቅ ሲሆን ይህ ሰፊና አደናጋሪ ትርጉሞቹን የያዘ ሕግ ሰላማዊ ተቃውሞን ከማፈኑም ባሻገር ለፖሊስ ኃይሉ የብርበራ፣የአሰሳና የማሰር ከፍተኛ ስልጣንን ሰጥቶታል።

በመሆኑም ዜጎች የተጫነብንን አፋኝ አገዛዝ ለማስወገድ እንዲሁም የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ነፃ ለማውጣት በጋራ እንነሣ።ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተረጋገጡባትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የድርሻችንን እንወጣ!

# ዓለም እውነት ያውራ!

**Mahider Geberegzi/ Wölfersheim**

ኢትዮጵያዊ ታሪካዊ ጀግናና የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት ሲሆን ለዚች ላለንባት ዓለም ውበቷም ባለውለታዋም ነው።ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ባለው ኢ-ፍትሃዊ ስርዓት ህዝቦች ለስደት ለእንግልት ለእስርና ለሞት እየተዳረጉ ናቸው።ይህን የማስቆም ደግሞ ሃላፊነቱ የኢትዮጵያውያን ብቻ አይደለም።የመላው አለምም ጭምር እንጂ። የዓለም መንግስታት በተለይ ሃያላኑ ለጋሾች በሚሰጡት እርዳታ በመታገዝ ህዝባችንን በማተራመስ ላይ የሚገኘው የወያኔ ስርዓት ዛሬ አይበገር መስሎ የሚታየው በእርዳታ ባገኘው የደለበ ሃብት ነው።ምዝበራው ጎሰኝነቱ ኢሰብዓዊ ድርጊቱ እረ ምኑ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል?

ዓለም መቼም በግሎባላይዜሽን አንድ ወደ መሆን በተቃረበበት በዚህ ዘመን በኢትዮጵያውያኑ ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ አይገነዘብም ማለት ይከብዳል።ስለዚህ ለአምባገነኑ ስርዓት የሚሰጠውን ድጋፍ በማቆም ደጋፍ የሚያስፈልገውን የሰፊውን ህዝብ በማገዝ ብሎም ከጎኑ በመቆም ይህችን አገርና ህዝቦቿን ከበለጠ ኪሳራና ውድመት ሊከላከል ይገባል።አገሪቷንና ህዝቦቿን የመታደግ ሃላፊነት የሰው ዘር መገኛዋ አገር ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ ከግንዷ ተወላልደው ዛሬ ከፍተኛ ኢኮኖሚ ያካበቱትም አገሮችና ህዝቦች ጭምር ነው የምለውም ለዚሁ ነው።

የዓለም ማህበረሰብ ለኢትዮጵያውያን ውለታውን መመለሰት ያለበት ወቅት አሁን ነው።ለዓለማችን ታሪካዊና ድንቃ ድንቅ ነገሮችን ላበረከተው ኢትዮጵያዊ ወያኔ ኢህአዴግን ለማስወገድ በሚያደርገው ትግል ከጎኑ ቆሞ ውለታውን በዚህ በሚፈልገው ወቅት መመለስና መካስ ይገባዋል።

ዓለም ይህንን ጥሪ ትቶ እንደለመደው ከስርዓቱ ጋር በመተባበር ሰብዓዊ ሃላፊነቱን ካልተወጣ ግን እንደ ቀደሙት አባቶቻችን ሁሉ ይህንን አስከፊ ስርዓት አፍርሰን የቀድሞውን ብዙ ክብራችንን በራሳችን ጀግንነት መመለሳችን አይቀርምና ያኔ እንዳንተዛዘብ!

የዓለም መንግስታትና የወያኔ ደጋፊዎች ሆይ ያኔ እናንተም ይህንን አሳፋሪ ድርጊት ባለማውገዝ ይልቁንም አይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆናችሁ ለፍርድ መቅረባችሁ አይቀርምና ሳይረፍድ የህዝብ ደም መፍሰሱን በየበረሃ በየባህሩ መሞትን በጀግንነት ጠብቆ ያቆየውን ማንነቱን ድንበሩን መሬቱን መቀማቱን በገዛ አገሩ እንደ 3ኛ ዜጋ መቆጠሩን ዜጎች ስለ ፍትህና እውነት የቆሙ የህዝብ ልጆችን የንፁሃን ጋዜጠኞች መታሰርና መሰቃየት ....... ብቻ ስቃይ በደል ሁሉ ይቆም ዘንድ አሳስቡ ከህዝብ ጎን ቁሙ! ሌላው ቢቀር የኣለም መንግስታት እርዳታ መስጠታችሁ ሳያንስ በትግላችን ላይ እንቅፋት መሆን አቁሙ! የወያኔ አባላትም ድጋፋችሁን በማቆም ህዝባችሁን ካሱ። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ለዘላለም ይኖራሉ!!!

# እባክዎ ዶክተር ወታደሮቹን ያግዱልን

**Tigist Kurabachew/Nürnberg**

ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም በትዊተር ገጻቸው የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን በተመለከተ የተቃውሞ ድምጾች መደመጥ መጀመራቸውን ዘግይተውም ቢሆን በማመን የመጀመሪያው ባለስልጣን ሆነዋል፡፡ቴድሮስ ፕላኑን መቃወም መብት መሆኑን በመናገር ተማሪዎቹ መደመጥ እንደሚገባቸው ይናገራሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ቢሆንም ቢያንስ የወጣቶች ህይወት እንዳይቀጠፍ መንግስታቸው በጠረጴዛ ዙሪያ ለመወያየት ዝግጁ እንደሚሆን አለመናገራቸው ያሳፍራል፡፡

የተማሪዎቹ ጥያቄ ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፕላኑ አገሪቱ ብዙ ወጪ እያወጣች ከምታስተምራቸው ለአገርና ለቤተሰቦቻቸው ተስፋ ከሆኑ ወጣቶች በላይ ዋጋ እንደማያወጣ የፕላኑ ባለቤቶች ማሰብ አለመቻላቸው አስጨናቂ ሆኖብኛል፡፡

ፈራሁ በጣም አድርጌ ፈራሁ መጪው ጊዜ እጅግ አድርጎ አሰጋኝ ጦርና የጦርነት ወሬ ጥላቻና ዘረኝነት ስጋ እየለበሰ ነፍስ ዘርቶ በሀገራችን ሰማይ ላይ እያንዣበበ ነው:: ከባድ ጥቁር ደመና የሚያስደነግጥ መብረቅ እያሰማ ዶፍ ዝናብ ሊጥል ነው:: አስፈሪው ጊዜ እየመጣ ነው የአንቦን ፀብ ሳንጨርስ የሀረርን ዜና ሰማን የሀረሩ ደሞ ይከፋል በጎረቤት ሀገርን የምንሰማው መጠፋፋት እየመጣ ይመስላል:: ፀሎትና ፍቅር በእጅጉ የሚያስፈልግበት ሰዓት ላይ ደርሰናል።:

# ኢትዮጵያዊያኑን ስደት ፈጃቸው

**Rahel Eshetu/ Würzburg**

በሶማሊያ እና በጅቡቲ እያደረጉ ቀይ ባህርን ወይም ህንድ ውቅያኖስን አቋርጠው ወደ የመን የሚገቡት ሰዎች ቁጥር በዚህ በያዝነው ሚያዚያ ወር በጣም ጨምሯል፡፡ በዛው መጠን መንግስትም ቁጥጥሩን አላልቶታል፡፡ በአዲስ መልክ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ጎዞው እየተጧጧፈ ነው፡፡ በቀን ሶስትና አራት ስደተኛ የጫኑ ጀልባዎች የየመንን ድንበር ይታከካሉ፡፡ ያራግፋሉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በአንድ ጀልባ ከ80 እስከ 90 የሚደርሱ ስደተኞች ይጫናሉ።ከሶማሊያ ቦሳሶ የምትባል አነስተኛ የወደብ ከተማ የሚነሳው ጀልባ ከ 36 እስከ 41 ሰዓት አካባቢ ይጓዛል፡፡ በዚህ መሀል ያላ አደጋ ስቃይ እንዳለ ሆኖ ጀልባው የመስመጥ እድል 50 ከመቶ የሰፋ ነው፡፡ በጅቡቲ በኩል ያሉት ተጓዦች ከሁለት አቅጣጫ የሚጫኑ ሲሆን አዩ በሚባለው ድንበር የሚወጡት ናቸው ወደ የመን ለመግባት ቅርብ እና የአራት ሰዓት ጉዞ የሚጠብቃቸው፡፡ ህገ-ወጥ አጓጓዦቹ ደግሞ በቅብብል እዚህ የመን ውስጥ ላሉት አጋቾች ገንዘብ ተቀብለው አስረክበው (ሸጠውላቸው) ነው የሚመለሱት፡፡ ሰሞኑን ከጅቡቲ ከተነሱት ሁለት የስደተኛ ጫኝ ጀልባዎች መካከል አንዱ ምን እንደነካው ሳይታወቅ ወደ የመን ድንበር ለመጠጋት በግምት ሁለት ኪሎ

ሜትር ያህል ሲቀረው ሞተሩ እንቢ ብሎ ሰጥሟል።

ሁሉም ገንዘብ ይታፈስበታል ወደ ተባሉት ግን ሞትና ስቃይ ወደሚታፈስባት ሳዑዲ ለመሄድ ነው ፍላጎታቸው:: በአይ.ኦ.ኤም መረጃ መሰረት ከሶማሊያ የሚመጣው ጀልባ በሚያራግፍበት ሽቡዋ በሚባለው የየመን ድንበር ብቻ ባለፈው ሳምንት ከ800 በላይ ስደተኛ ገብቷል:: ከጅቡቲ የሚመጡት በሚራገፉት ባብል መንደብ አካባቢ ደግሞ ከ600 ያላነሰ ሰው እንደገባ ነው:: እልቂታችን እስከመቼ ይቀጥላል… ሀገር እያለን እንደሌለን ሀገር አልባ ህዝብ ሆነንስ እስከመቼ? ታዲ ይሄን ችግር ማን ፈጠረው ለምንስ ነው ህዝብ በስደት ሲያልቅ ወያኔ ኢህአዴግ ዝም የሚለው? መብቱን በመጠየቅ እስትፋሽ የነሳውን ህዝብ መበቀያ ቅጣት እያደረገው ነው። ወገን እስከ መቼ ይሆን ትዕግስታችን? ቢያንስ ራሳችንን ማዳን ያቅተን?

# አብዮታዊ ፕሬስ የለም።

**Yohannes Selamu/ HOF**

የነፃ ፕሬሱ ሰዎች ምን ያልመጣባቸው መዓት አለ? ይባስ ብሎ ትንሽ ነገር በተነሳች ቁጥር የወሬ ጦማሪዎችን እስር ቤት ማጎሩ ዛሬም የተለመደ የኢህአዴግ ምስ ሆኗል።

የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት የሚከተለው የአብዮታዊ "ዴሞክራሲ" ስርዓት አብዮት ልጆቿን ሁሉ ከመብላት እንደማትመለስ ያስመሰከረ ከሆነ ውሎ አድሯል። ኢህአዴግ ራሱ በፈጠረው ችግር ዜጎች በአደባባይ ለግድያና ለአካል መጉደል ችግር እየተዳረጉ ይገኛሉ። በቅርቡ በኦሮሚያ ወጣቶች ላይ የደረሰው ግድያና አካል ጉዳት የስርዓቱ ፖሊሲ የፈጠረው ችግር ነው። እንዲህ አይነት ችግሮች ሲከሰቱ ለዓለም የሚያሳውቁትን ጋዜጠኞች ቀድሞ ምክንያት እየፈለጉ ማሰርና ማጎር ምን አመጣው? ወይም አገሪቱ ህግና ስርዓት አይገዛትም ብሎ ማወጅና ወንጀሎችን ህጋዊ ማድረግ አሊያም በስርዓት ከመጓዝ ውጭ ኢህአዴግ ራሱ ህጋዊነትንና ህገወጥነትን እያደባለቀ መሄድ አይችልም።

ሁሉንም ነገር በአብዮታዊ ስልት ጠፍሮ የያዘው ኢህአዴግ ብሎ ብሎ ፕሬሱም አብዮታዊ እንዲሆን እየሰራ ይገኛል።ችግር ሲነሳ የውሸት ሪፖርት የሚለፍፉትን ካድሬዎች እያሰማራ ግራ ከማጋባቱም በላይ ራሱን ላይ ላዩን በመቀባባት ሰላማዊ መንግስት ለመምሰል የሚያደርገውን ጥረት ከፕሬሱ እኩል እያንዳንዳችን የማጋለጥ ሃላፊነት አለብን። ሰላም ለኢትዮጵያ!

# ትግላችንን እናስተሳስር!

**Roza Teshome/Würzburg**

የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን ሃይል ማስተሳሰር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አይሆንም።የትስስሩ ዓላማ ሁሉም ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ሃይሎች አገርቤት ይሁን ውጭ፣ በትጥቅ ትግል ይሁን በሰላም የሚታገለውን ሁሉ በጋራ በመቆም እንዲታገልና ያለውን ስርዓት አስወግዶ በዲምክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን ለህዝብ የሚሸጋግርበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነው::

ስለሆነም አሉ የተባሉትን ታጋይ ኃይሎች ለማጣመር መስራት ያስፈልጋል:: አገር ቤት ካሉት ታጋዮች ጋር በግልጽ ሊደረግ የሚችል ግኑኝነት አሁን ባለው ሁኔታ ላይመች ይችል ይሆናል ግን መንገድ ከተፈለገ የማይኖርበት ሁኔታም የለም። ትግሎቻችንን ግን ማቀናጀት እንችላለን:: ዋናው የትግል ሜዳ በአገር ውስጥ መሆኑን እገነዘባለሁ።

አገር ቤት ያለው ስርአቱን ፊት ለፊት በመጋፈጥ መስዋእትነትን ሲወስድ በውጭ ያለው ደግሞ ለትግሉ ደጋፊ የሆኑትን የዲፕሎማሲ፣ የገንዘብና የማቴሪያል ካስፈለገም የትጥቅ፣ የሚድያ፣ የምልመላ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል:: ስለዚህ የዳበረ አቅም እያለን የቀረን መከባበርና መቀናጀት በመሆኑ ለጋራ ትግል በጋራ እንነሳ የሚል ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

# በዩኒቨርስቲዎች ተቃውሞው አይሏል

**Firezewed Berhanu/Fulda**

የከፋ ጉዳት የደረሰው በአምቦ፣መደወላቦ እና ሐረማያ ቢሆንም ተቃውሞው በመንግስት ሚዲያ ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይነገር ታግዶ ነበር።

አዲስ አበባንና በዙሪያዋ የኦሮሚያ ከተሞችን በማካተት የተዘጋጀውን የጋራ ማስተር ፕላን የሚያወግዙ የክልሉ ተማሪዎች፤ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ሲያካሂዱት በሰነበቱት ተቃውሞ በሳምንቱ አጋማሽ ላይ ከፖሊስ ጋር በተፈጠረ ግጭት የበርካታ ሰዎች ህይወት ጠፍቷል:: በትንሹ ወደ መቶ የሚጠጉ ሰዎችም እንደቆሰሉና ጉዳት እንደደረሰባቸው መንግስትም በአምቦና በመደወላቡ 3 ተማሪዎችን ጨምሮ 7 ሰዎች እንደሞቱ አምኗል። ሲኤንኤንና ሌሎች የሚዲያ ተቋማት በርካታ ሰዎች መሞታቸውን በመጥቀስ የተለያዩ ዘገባዎችን ያሰራጩ ሲሆን የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ 30 ሰው መሞቱን እንደተናገሩ ጠቅሰዋል:: የእግር ኳስ ጨዋታ በቴሌቭዥን የሚመለከቱ የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ በተወረወረ ፈንጂ አንድ ተማሪ እንደሞተና 70 ሰዎች እንደቆሰሉም መግለጫው አስታውሶ፤ ዩኒቨርስቲዎች እንደተረጋጉ መንግስት ቢገልፅም በስልክ ያነጋገርናቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን ግን ግጭቱና ውጥረቱ እንዳልበረደ ተናግረዋል::

በአዳማ፣ በጅማ፣ ሃሮማያ፣ አምቦ፣ ነቀምት፣ መደወላቡ እና ድሬደዋ ዩኒቨርሲዎች በተነሳው ተቃውሞ እስካሁን ከተገለጸው በላይ የሞትና የአካል ጉዳት በተማሪዎች ላይ እንደደረሰ የየአካባቢው ምንጮች የገለፁ ሲሆን፣ በርካቶች እንደታሰሩም ጠቁመዋል:: በሃሮማያ ፍንዳታ የሞቱት ተማሪዎች ሁለት መሆናቸውን የገለፁ ምንጮች፣ በብሄር ተወላጅነት የተቧደኑ ተማሪዎች ጎራ ለይተው በፈጠሩት ግጭት በርካታ ተማሪዎች እንደተደባደቡ ተናግረዋል::

ስለዚህ የወያኔ ኢህአዴግ ስርዓት ምንኛ ችግር እንዳለበት ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ይቀርባል።ህዝብን የናቀ ራሱ ይናቃልና ነገሩ ወገኔ ሆይ ተሰባስበንና ተደራጅተን ስርዓቱን ለመናድ ሁላችንም ሃላፊነታችንን እንወጣ!

# የመከኑ ቃሎች

**Yared Taddesse/HOF**

ኢትዮጵያ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች፣ በቀን ሦስት ጊዜ ትመገባላችሁ ስደት ይበቃል. . . ኢህአዴግ ስልጣኑን ለመቆናጠጥ የገባልን መካን ቃል ነበር። ወያኔ ኢህአዴግ ፍትህዊ ልማት ማምጣትና ድህነት መቀነስ ተቀዳሚ ተግባሬ ነውም ብሎን ነበር። ነገር ግን የተወሰኑ መሠረተ ልማቶችን ከመገንባት ውጪ ኢኮኖሚው ከግብርና ወጥቶ ወደ ኢንደስትሪው አልተሸጋገረም። ዛሬም ከአምስቱ ዜጎች አራቱ በድህነት ላይ የሚገፉው አርሷደሮች ናቸው።ዋና

ከተማዋን ጨምሮ አብዛኛው ህዝብ መብራት የሚያውቀው የሰው ስም መሆኑን እንጂ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ሆኖ አይደለም።ለጎረቤት አገር ጂቡቲ ሱዳንና ኬንያ ግን ኤሌክትሪክ ኤክስፖርት አድርገን ገቢ ልናገኝ ነው እየተባልን እንዲሁ እየደነቆርን ነው።አበው የራሷ አሮባት.......አሉ።

ንጹሕ የመጠጥ ውሀ ለማግኘትም እግዚአብሔር ዝናቡን ሲሰጥ እየጠበቁ ወደ መጠጣት ተደርሷል።ሁሌም ችግር አለ ሲባሉ ገዢዎቻችን እረ በከፍተኛ መጠን አሳድገነዋል እያሉ ይደሰኩሩልናል።ከሦስቱ ኢትዮጵያዊ አንዱ እጅግ በጣም ያጣ የነጣ ነው። አሁንም መንግስት ከ5 ሚሊዮን ለማያንሱ ዜጎች በየአመቱ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ይለምናል። ዛሬ አብዛኛው ሕዝብ በቀን ሦስቴ መብላት አይደለም በቀን አንዴ ለመመገብ እየተቸገረ ነው።

በእርግጥ ሥርዓቱ ሀብታም ያደረጋቸውና ከገዢው ፓርቲ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በአንድ ሌሊት ከድህነት ወጥተው ሀብታም እየሆኑ ነው። አልፎም ከሙሰኛ ባለሥልጣናት ጋር አብረው እየነገዱና እየዘረፉ በሀገር ውስጥም በውጪም እያጠራቀሙ ነው። ከመልካም አስተዳደር ችግር፣ ከድህነትና ከነጻነት ማጣት የተነሳ በየአመቱ በአማካይ ከ250,000 በላይ ዜጎች በሕጋዊና ሕገ ወጥ መንገድ ይሰደዳሉ። ብዙዎቹም በመንገድ ላይ ይሞታሉ፣ የውስጥ አካላቸው ይሰረቃል፣ ወደ አረብ ሀገራት የሚሄዱት ደግሞ የሚደርስባቸው በደልና ግፍ ብዙ ነው። ዛሬ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በኬንያና በሱዳን የስደተኞች ጣቢያ ይገኛሉ። በአጠቃላይ ከ23 አምታት በኋላም ሀገሪቱ ከ1983 በፊት እንደነበረችው በአምባገነኖች ስር ነች። የሕግ የበላይነት የለም። ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የማይታሰብ ነው። የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመሳሰሉት መብቶች በገዢው ፓርቲ መልካም ፍቃድ ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው። ስለዚህ በኢትዮጵያ አመጣዋለሁ ብሎ ወያኔ ኢህአዴግ የደሰኮረው ቃል ተመልሶ ላይስተካከል መክኗል። ሌላ 23 ዓመት ወይስ 23 ወር እንታገስ?አይበቃንም ወገኔ?

# ፓርቲያችን ይጎልብት!

**Dawit Mamo/ Aschaffenburg**

**እስኪሰፍን ድርስ ፍትህ ነፃነት**
**እንታገላለን ሆነን በአንድነት**
**ጭቆና መረገጥ መታፈን መታሰር**
**በጎሳ በሃይማኖት መለያየት በዘር**
**እስኪጠፋ ድረስ በአንድነት**
**እንቁም**
**ፓርቲ ያችን ኢህአፓ ይኑር**
**ለዘላለም**
**ኢህአዴግ ወያኔ መርዝ ነው ላገሬ**
**ይህ ደሞ ሓቅ ነው ትናንት ሆነ ዛሬ**
**ይጥፉ ከምድሪቱ ተነቅሎ ከስሩ**
**ይኑር ያለስጋት ህዝቡ ባላገሩ**
**እስከመቼ ድረስ አፋችን ታፍኖ**
**የህግ የበላይነት በቃል ተሸፍኖ**
**የዘር ማጥፋት ተግባር ከምድራችን**
**ይጥፉ**
**የሰው መብት ይከበር ፍትህ**
**ይስፈን ይስፋ**
**ኻያ ሁለት ዓመታት  አንድ ኹለት**
**እያልን**
**መቁጠሩን አቁመን እንቁም**
**ባንድነት**
**ትግላችን ይጠንክር ፓርቲያችን !**
**ይጎልብት!!!**

# ከእኛ ምን ይጠበቃል?

**Arsema Yonas/ Erlangen**

በውጭም ይሁን በአገር ውስጥ ካለን ኢትዮጵያውያን የሚጠበቅብን ግልፅና አጭር ነገር ነው።እነዚህንም እንደሚከተለው አቀርባቸዋለሁ።

1ኛ/-በኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዓላዊነት፣እንዲሁም በአገሪቱ የግዛት አንድነት ላይ ግልጽና የማያወላውል እምነትና አቋም መያዝ፣
2ኛ/-የማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ማክበር፣በየድርጅቶች ውስጥና በምንሰባሰብበት የህብረት ማዕቀፍ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ግንኙነቶችንና አሠራሮችን በማስፈን መስራት፣
3ኛ/-በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ፀንቶ መታገል
4ኛ/-በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ምንም አይነት አድሏዊነት እንዳይኖር ሁሉም ዜጋ እኩል መሆኑን ማመንና በተግባርም ማረጋገጥ፣
5ኛ/-የህወሃት/ኢሕአዴግ መንግሥትና ሥርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት በመሆኑ መለወጥና በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መተካት እንዳለበት ማመን፣

በተጠቀሱት ዓላማዎች ዲሞክራቲክ ኃይሎችን በማሰባሰብና በጋራ በመታገል ያለውን ስርዓት አስወግዶ ሁሉንም በዲሞክራሲያው መንገድ ሊያሳትፍ የሚችል የሽግግር መድረክ ተፈጥሮ ዲሞክራሲያዊ መድብለ ስርዓት እንዲፈጠር መስራት ነው፡፡ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# ኢትዮድያ:- ሰው እንደጎመን በቀላሉ የሚቀጠፍባት አገር

**Mikyas Befekadu /Mental**

የወያኔ መንግስት ማህላ ፈፅመው ስልጣን ከያዙ በኋላ እንኳ ብዙ ንፅሀን ዜጎች በነጻ እርምጃ ተገለዋል።

ያለጥፋታቸው ዜጎች በገፍ እየታሰሩና ስቃይ እየተፈፀመባቸው ነው። የታዘለች ህፃንም አልቀረላትም። ይህን አይነት መንግስታዊ ሽብር በሚፈፀምበት አገር ለአፍ ካልሆነ ፖለቲካ ማህደሩ ሰፍቷልም ጠቧልም ብሎ መከራከር ልብ ድከም ማድረግ ነው። በጠቅላላው የስልጣን ዘመናችሁ የፈፀማችሁት ፍጅት ቢወዳደር ከደርግ የሚብስ ይመስለኛል። ምክንያቱም በዚህ ደረጃና በማያባራ ሁኔታ በየቀኑ በግፍ ስለሚገደሉ ስለሚታሰሩ ሰቆቃ ስለሚፈፀምባቸው ንፁሀን ዜጎች የማይገደው መንግስት ነው ያለው። በርግጠኛነት ግን እስቲ ቦንብ አፈንድተን ሀያ ሰላሳ ሰው እንግደልና የዜጋውን ስሜት እናጥና ወይም ፖለቲካ እንስራበት ብለው ፍጅት የሚፈፅሙ መሪዎች አልነበሩም።

ደርግም አንባገነን ስርአት ስለነበር ሰፈራ የመሳሰሉ ግብታዊና ጎጂ እቅዶችን ተግባራዊ አድርጓል። ዜጎች ያልተስማሙባቸውና አምርረው የተቃወሟቸው ቢሆንም እንደ ወያኔ መንግስት ያጉረመረመውን ሁሉ በገፍ የሚገድል ግን አልነበረም። ህንፃ

የሆነው። ይህ የባህሪያችሁ ከመሆኑም በተጨማሪ ከፍተኛ የማስተዳደር እውቀት ችግር ባለቤት መሆናችሁ የአደባባ ሚስጢር ነው።። ክብር ለሆነው የሰው ልጅ ሂወት የሚሰጠው ዋጋ ቀሎ ከመቸውም ጊዜ በባሰ መልኩ እየታየ ይገኛል። ሞት ለወያኔ። ክብር ለሰምእታት።

# የኢህአዴግ መንግስት ዜጎችን ማሰቃየቱን ቀጥሏል።

**Jemal Awel /Ehringshausen**

ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ገዢ ነኝ ካለበት ጊዜ ጀምሮ ህዝብን ያስቀየሙ፣ ያሳዘኑና፣ ያሳፈሩና ቂም ያስቋጠሩ ተግባራትን በግልጽና “በድብቅ ግን የሚታወቅ” አከናውኗል። በተለያዩ ጊዜያት በተግባሩ የተነሳበትን ተቃውሞ ለማፈን ሃይል ተጠቅሟል። አልሞ ተኳሾችን አሰማርቶ ዜጎችን ልባቸውና ግባራቸው አየተመታ እንዲገደሉ አድርጓል። የሚችለውን ያህል አስሯል። ገርፏል። ራሱ ክስ መስርቶ ራሱ እየፈረደ ወህኒ ወርውሯል። ነጻ ፕሬስን ሰቅሎታል። ሃሳብን በነጻ ማራመድን በህግና ህግ በማይጠቀስበት አግባብ አግቷል። አሁን ኦሮሚያ ላይ የተነሳውን የተቃውሞ አመጽ ተከትሎ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ በጥበብ ከማስተናገድ ይልቅ ብረት አንስቶ መግደልን መርጧል። ኢህአዴግ በገደለ ቁጥር አገሪቱ ስጋቷ እየጨመረ፣ የህዝብ ስሜት እየተበላሸ ነው። ይህ እንደሚዲያ ያስጨንቀናል። ኢህአዴግ የዘራው የቂም ዘር በየአቅጣጫው ፍሬው እየጎመራ መሄዱ ያሳዝነናል። ከሁሉም አቅጣጫ መፍትሔ የሚፈልግና ችግር የሚያረግብ አይታይም። አገሪቱ አስተዋይ በማጣቷ በስጋት ደመና እየነፈረች ነው። የአንዱ ለቅሶ ለሌላው ደስታ እየሆነ ነው። ከዚህ በላይ የሚያስጨንቅ ምን አለ? አማራው፣ ደቡብ ክልል ያሉ ዜጎች፣ ኦጋዴን፣ ሶማሌ፣ ሁሉም ጋር ብሶት አለ። የኑሮ ችግር የጠበሳቸው የበይ ተመልካቾች መሯቸዋል። ያልመረራቸው ቢኖሩ ከቁጥር የማይገቡ ባለጊዜዎች ብቻ ናቸው። ይህም ታላቅ ስጋት ነው!!

# ኢህአዴግ ተቃውሞና የተቃውሞ ድምጽ ያስበረግገዋል

**Saba Tekilu/Schlüchtern**

አዎ!! ኢህአዴግ የተቃውሞ ድምጽ ሲሰማ ይርዳል። የተቃውሞ ድምጽ ሲሰማ ይንቀጠቀጣል። ሲቃወሙት የበረሃ ወባው ይነሳበታል። ከድንጋጤው የተነሳ ይበረግጋል። ይደነብራል። ለምን? ቢባል በደም የተለወሰ ፓርቲ ስለሆነ ነው። ኢህአዴግ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ነፍስ ያላጠፋበት ስፍራ የለም። በመሀል አገር ክቡር የሰው ልጆችን ገሏል። የሚደመደም ነገር ባይኖርም በበላዮቹ ትዕዛዝ ኢህአዴግ ባፈሰሰው ደም መጠን ጠላት አፍርቷል። ወዳጁና አጋሩ ጠብመንጃና በደም የለወሳቸው አባላቱ ብቻ ናቸው። ሌላ ወዳጁ እንዳሻው የሚዘራው የአገሪቱ ሃብት ነው። የህዝብ ሃብት ህዝብን ለማፈን ማዋል ሌላው ስጋቱን ለመጥቀስ እንጂ ከዘርፊያ ጋር የተቆራኘውን ታሪኩን ለመዘርዘር አይደለም። ስለዚህ ህዝብ ሲቃወም ያጥወለውለዋል። ይጓጉጠዋል። አውሬ ይሆናል። ህግና ስርዓት አፍርሶ የጫካ ደንብ ይተገብራል። ባጭሩ ይገላል!! ኢህአዴግ የድሃውን ገበሬ መሬት ከመሸጥ ይቆጠብ። መቃወም ህጋዊ መብት ስለሆነ ኢህአዴግ ተቃውሞን ከመፍራትና እመራቸዋለሁ የሚላቸውን ወገኖች ከመግደል ይልቅ ህዝብን የሚያስቆጣ ተግባር ከመፈጸም ራሱን ያቅብ።

# ብአዴን አማራ አይደለም።

**Theodros Admasu/Mental**

በሀረማያ ዩንቨርስቲ የኣማራና ሌሎች ተወላጆች ኳዋስ በሚያዩበት ወቅት የተቀበረ ፈንጂ ፈንድቶ ኣንድ ሰው በኣሰቃቂ ሁኔታ ሲሞት ከመቶ ሀምሳ በላይ ከባድና ቀላል የመቁሰል ኣደጋ ደርሶባቸዋል። ቦንቡ የተቀበረው በዛው ክልል ተወላጆች ወይም በኦሮሞና በኦህዴድ የሚታገዙ እንዲሁም የዩንቨርስቲው ኣስተዳደር ይገኙበታል። ቦንቡ ከመፈንዳቱ በፊት በኦሮምኛ ቋንቋ ውጡ የሚል ድምጽ ይሰማል ። ከዚያም የወጣው ወጣ የተቀረው ከኦሮሞ ወጪ ተወላጆች በዚህ ኣሰቃዊ ኣደጋ ሰለባ ሆነዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የኦህዴድ ኣባላት በኣማራ ተወላጆች ላይ ጣት የመቀሰርና ለተፈጠረው ብጥብጥ መንስዔ ለማድረግ ደፋ ቀና እናሉ ይገናሉ። ይህንን በመሸሽ ዛሬም በየቤተ ክርስትያኑ ተጠልለው ሚላስ ሚቀመስ ኣተው ግማሹ ደግሞ ተሳፍሮ ወደየ ቀዩ በመሄድ ላይ ይገኛል።

23 ኣመት ሲጋገር የነበረው የዘር ፓለቲካው ዛሬ ባለንበት ዘመን ደርሶ ለማየት እየበቃን ነው። የኣኖሌ ሀውልት ውጤት ማምጣቱ ኢሃዴጋውያን በእጅጉ ደስተና ደስተኛ ኣድርኝቸዋል። ልብ በሉ ለኣማራ ቆሚያለሁ ያለው ብአዴን ኣፉን ዘግቶ ተቀምጡዋል።ኣማራ 23 ኣመት ሙሉ ሲሰቃይ ኣንዳችም ነገር ያላለ ዱዳ ድርጅት ነው ብንለው ምን ያስቀይማል። እውነት ብአዴን ለኣማራ ተቆርቋሪ ነውን?ወይስ ኣማራ እንዳይጠናከር ጠንክሮ የሚሰራ ? ይህ ጥያቄ ለዘመናት ያልተመለሰ ከመሆኑ ኣንጻር ባለፈው በስብሰባ ኣዳራሽ የብአዴን ኣመራሮች እኛን ሲሰድቡና ሲያዋርዱ እንደሰማነው በተይያዢነት

ለመግንባት፤ መንገድ ለመስራት፤ አበባ ለመትከል የንፁህን ሂወት እስርና ስቃይ የግንባታዎቹ ሁሉ መሰረቱ እኮ ነው መልሱንም ያገኘነው ይመስላል። የብአዴን ኣመራሮች በትውልደ ትግሬና ኤርትራዊ የሆኑ መሆናቸው በኣማራው ላይ በየጊዜው ለሚደርሰው በደል ቅር የማይሰኙና ከኦህዴድ ሰዎች ጋር ኣብረው ተቀናጅተው ኣማራን ፈጽሞ በማጥፋት ላይ ይገኛሉ። ኀበዝ ካንቀላፋህበት ንቃ ለራሳችንን ህልውና ስንል ዘራችንን እናስከብር።

# አፈናና ግድያ ትግሉን አያስቆመውም።

**Meseaily Dedjnie/ Alsfeld**

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲሁም የተፈጥሯዊ ሃብቱ ባለቤት ሆኖ ሰላም የሰፈነባት ህፃናት የሚቦርቁባት አረጋዊያን የሚጦሩባት ወጣቶች የሚዳሩባት ሆና እንድትቀጥል በየዘመናቱ ዜጎች ክብር መስዋዕትነት እየከፈሉ ጥያቄአቸውን አንግበው መታገላቸውን አላቆሙም ።አንድ አምባገነን ሲወድቅ ሌላው እየተተካ የህዝቡን የፍትህ የሰላም የዴሞክራሲና የልማት ጥያቄ ምላሹ ግድያ መሆኑ ዛሬም አልተቀየረም።የዚህም ችግር ዋነኛ ምንጩ በህዝብ ይሁንታ የተመረጠ መንግስት ባለመኖሩ የህዝቡን ጥያቄ አዳምጦ መልስ መስጠት አለመቻሉ ነው።

ነገር ከምንጩ እንዲሉ ትግሉን በስፋት በማቀጣጠል መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በዘር በጎሳ በሃይማኖት ሊከፋፍሉትና አንድነቱን ሊሸረሽሩት በሚችሉ ማንኛውም አደጋ በመጠንቀቅ የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ለኑሮ ውድነት ለእንግልት ለስቃይ ለስደት ለእስራት ግርፋትና ሞት የዳረገውን ስርዓት ለመጣልና ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት በንቃት መታገል ይኖርበታል።

የህዝቡን ትግል ለማጨናገፍ ካድሬዎቻቸውና የነሱ የሆኑ ሚዲያዎች ድንጋይ ዳቦ ሆነ ወዘተ የመሳሰሉትን ዘመቻዎች ቢከፍቱም ሰሚ ጆሮ በማጣታቸው ስልታቸውን ቀይረው ተቃዋሚዎችን መከፋፈል የተለመደ ሴራቸውንም በመገንዘብ ጠንክሮ መታገልና ከስር መሰረቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወያኔን መንቀልና ለውጥ ማምጣት ብቸኛ መፍትሄ ነው። ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

# ኢትዮድያ፡- በወያኔ በጎፈቃድ የምትመራ አገር

**Girum Kelemu and Nethanet Mamo /Gross gerau**

ለከት ያጣው የወያኔ ጭካኔ እና የማይነጥፈው የሕዝብ ትእግስት ኢትዮጵያን ወዴት እየወሰዷት እንደሆነ አገሪቱ ዛሬ ያለችበት ውጥንቅጥ ሁኔታ በግላጭ ያሳያል። በመግደል አባዜ የተለከፉት የወያኔ ተጋዳላዮች ዛሬም መግደላቸውን ቀጥለዋል። ለይስሙላ በወረቀት ላይ የሰፈረው ሕገ-መንግስት እና በውስጥ የያዛቸው መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶችና ነጻነቶች ለወያኔ ተጋዳላዮች ምናቸውም እንዳልሆነ በተደጋጋሚ እያሳዩን ነው። በአገሪቱ ውስጥ ያለው የሕግ ማእቀፍ (አንዳንዶቹ ሕጎች በራሳቸው የማፈኛ መሳሪያ ተደርገው የተቀረጹ መሆኑ ሳይረሳ) ለወያኔ ተጋዳላዮችና ተራ ካድሬዎች ሳይቀር ምናቸውም አይደለም። ሲሻቸው ይገድላሉ፣ ያፍናሉ፣ ይሰውራሉ፣ ባደባባይ ይደበድባሉ፣ ሺዎችን በየማጎሪያው ያሰቃያሉ፣ ያዋርዳሉ፣ ቅጥ ባጣ መልኩ ይሞስናሉ፣ ይሰርቃሉ፣ ይዘርፋሉ፣ ያስፈራራሉ፣ ሴቶችን ይደፍራሉ፣ ህዝብን ያሸብራሉ፣ ምኑ ቅጡ። እንግዲህ የሕግ አምላኩ ሲሞት ሥርዓት አልበኝነት ይነግሳል፤ ዘራፊዎች ይበራከታሉ፣ ገዳዮች ባደባባይ ገድል ይጥላሉ፣ ሙሰኞች አገርን እና ሕዝብ ይቆጣጠራሉ፣ የአገር ሃብት ያሸሻሉ፣ በድሆች ጉሮሮ ላይ ቆመው በሃብት ይጨማለቃሉ። በዚህ ላይ ጎጠኝነት ሲታከልበት መላ ቅጡ ይጠፋል። ብዙዎቹ እየከሰሙ ያሉ አገሮች (failed states) እየተባሉ በየጊዜው የሚጠቀሱ አገሮች በእነዚህ ችግሮች ውስጥ የሚማቅቁ ናቸው። ወያኔም ለኢትዮጵያ የዋለላት አንዱ ትልቁ ነገር ከእነዚህ አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ማድረጉ ነው። እንደ ታላቅ ስኬት የሚቡተለከለት የዛሬዋ የኢትዮጵያ ልማት ውስጡ ሲገባ ላዩ አሮ ውስጡ ሊጥ እንደሆነ ዳቦ ስለመሆኑ ምንም ጥናትና የተለየ ምርምር ሳይጠይቅ 95% የሚሆነውን የአገሪቷን ሕዝብ ኑሮ ማየት በቂ ነው። አንጻራዊ በሆነ መልኩ በወያኔ ዘመን የመጀመሪያዎቹ አሥር አመት ውስጥ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኛቸው የነበሩትን እንደ መብራት፣ ውኃ፣ የጤና አገልግሎትና ሌሎች መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ዛሬ ተነፍጓል።ኢትዮድያ በተባበረ ክንድ የህግ ባለቤት ትሆናለች!!!

# አይ አለመታደል

**Belay Fikre /Ehringshausen**

የደብል ዲጂት ልማታዊነት ነጠላ ዜማዎች በወያኔ እና ባጫፋሪዎቹ የአለም አቀፍ ‘የልማት’ ተቋማት ጆሮዎችን እሲደነቁር በሚዘፈንበት በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አስከፊ በሆነ የኑሮ ዋስትና ማጣት ውስጥ ሆኖ የመከራ እንቆቅውን እየተጋተ ይገኛል። የእነዚህ የመሰረታዊ አቅርቦቶች በዚህ ደረጃ ላይ አቀልቁሎ መገኘት እንኳን የቀለም አብዮት፤ ሌላም መገለጫ የሌላቸው አመጾችንና እልቂትን ቢወልድና በአገሪቱን ወደ ከፋ ብጥብጥ ቢከት የሚገርም አይደለም። ይሁንና እንደ ወያኔ ያለ ክፉ፣ መረን የማያውቅ እና ጨካኝ ሥርዓት እድለኛ ሆኖ ሆደ ሰፊ፣ የማይቻለውን ሁሉ የሚችል፣ ጨዋና ታጋሽ ሕዝብ

ሲያጋጥመው ጭካኔውን እያበረታ፣ የአፈና ሰንሰለቱን እያጠበቀ፣ አባላቱን በአሃብት እያሞሰንነና እያጎለበተ ይንሰራፋል። የአገር መፍረስ ወይም አደጋ ላይ መወደቅ የራሳቸውን ጥቅም አደጋ ላይ እስካልጣለ ድርስ ግድ የማይሰጣቸው ጎጠኛ ፖለቲከኞችም በደሃው ሕዝብ ላይ ይሰለጥኑበታል፤ ይሰይጥኑበታልም።ህዝብን የሚያከብር፣ ለህዝብ ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በህዝብ የሚምል፣ ህዝብ ውስጥ የሚኖር፣ ህዝብ እውቅና የሰጠው፣ ህዝብ የሚያምነው፣ ሲፈልግ የሚቀጣው፣ ሲፈልግ የሚያሞግሰው አስተዳደር አጋጥሞን አያውቅም። የቀደመውን ኮንኖ የሚመጣው ከቀደመው የማይሻል፣ ደም የጠማው፣ ጠመንጃ አምላኩ የሆነ አገዛዝ ነው። አገሪቱም፣ ትውልዱም፣ የወደፊቱ እንግዳ ዘርም ሁሉም በስህተት ቅብብል በርግማን ይኖራሉ። ነፍጠኛ፣ ትምክተኛ፣ ጎጠኛ፣ ጠባብ፣ ኪራይ ሰብሳቢ፣ አንጃ … ቃላት እንደ ፋብሪካ ምርት እየተፈበረኩልን ስንሰዳደብ እንኖራለን። እንደ አለመታደል የሁሉም አስተሳሰብ አንድ ብቻ ነው – የራሱን ህልውና ለማስፈን የሚቃወሙትን ሁሉ መደምሰስ! “በጠላቶቻችን መቃብር ላይ …” የሚለው መፈክር ደርግ ቢለውም የራሱ በማድረግ አንግቦ የሚዞረው ግን እጅግ በርካታ ነው፡፡የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሩቅ አይሆንም!!!

# ምርጫ 2007 ከወዲሁ ሲቃኝ

**Eden Dawit Kidane /Gießen**

ምርጫ 2007ን በምን መልኩ ትጠባበቃላችሁ ብትባሉ ምን ብላችሁ ትመልሳላችው? መቸም በጉጉት የሚል ባይጠፋም ቁጥሩ ጥቂት እንድሚሆን እገመታለሁ። ለዚህ ከሚቀርቡ ምክንያቶች ጥቂቱን ጀባ ልበላችው። በመጀመርያ ግን ስለምርጫ አስፈላጊነትና ምንነት ማውጋቱ አስፈላጊ ነው። በጥቅሉ ሁሉም ሰው የምርጫን አስላጊነት ያምናል። ግን ምርጫ ለምን ያስፍልጋል? በመሠረቱ አንድ አገር በምርጫ ብትተዳደር ለመልካም አስተዳደር : ለልማትና : ብልጽግና ጠቃሚ ነው። ለሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጻኦ ያደርጋል። ለዜጎችም የፈለጉትን ድርጅትና መሪ እንዲመርጡ እድል ይሰጣል። ከምርጫ ውድድር ውጭ ወደ ስልጣን የሚመጣበትን መንገድ ይገድባል። በህብረተሰብ ውስጥ ሁለገብ ዲሞክራሲ ከሰፈነ : መልካም አስተዳደርና ፍትህዊነትም ካለ : ዜጎች በእኩልነትና በአሳታፊነት የሚተዳደሩ ከሆነ ድህነት ቢኖር እንኩዋን ሰርቶ ለመለወጥ ተስፋ ስለሚያደርጉ ባገኙት ሰላም ተረጋግተው ይኖራሉ። ከስደት ይልቅ በአገር መኖርንም ይመርጣሉ። ከዚህ እንጻር እነዚህ ምክንያቶች ለአገራችን የምርጫን አስፈላጊነት ማሳያ በቂ ናቸው።

ታድያ ምርጫ 2007ን ስናስብ ከዚህ አንጻር መሆን ይኖርበታል። በመሆኑም ፓርቲዎች በምርጫ ሲሳተፉ ምን ታሳቢ አድርገው ነው? ሕዝብስ ሲመርጥ ምን ታሳቢ አድርጎ ነው? እኔ እንደማስበው ፓርቲዎችም ይሁኑ ሕዝብ ከላይ የተገለጹትን የዴሞክራሲ እሴቶች ተማምኖ አይደለም። እነዚህ እሴቶች በአገራችን እንደሌሉ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ምርጫ ከምርጫ ሂደትና የፖልቲካ ምህዳር ተለይቶ ኣይታይም። የፖለቲካው ምህዳርና ሂድቱ በራሱ ሁሉንም ተወዳዳሪዎች እኩል የሚያስትናግድ ካልሆነ የምርጫው ውጤት በራሱ የዴሞራሲ ስርአትን መኖር ማራጋገጫ አይሆንም። ሂደቱና ውጤቱ ትክክል የሚሆኑትና በሁሉም ተወዳዳሪዎች ተቀባይነት የሚኖረው በሂድቱ እኩል ተሳትፎ ሲኖራቸው ብቻ ነው። በዚህ መስረት እስቲ የ2007ን ምርጫ እንገምግም። እንደሚታወቀው ከ1997 ቦሃላ የፖለቲካውን ምህዳር የሚያጠቡ ብዙ ሁኔታዎችና ህጎች ተከስተዋል። የመያዶችና የሲቪል ማህብራት እንዲሁም ነጻ ፕሬስን የሚመለከቱትን ህጎች ማስታወሱ በቂ ነው። እነዚህ ህጎች ለፓርቲዎች እንቅስቃሴ ወሳኝ ናቸው። ፓርቲዎች እንደፍላጎታቸውና በሙሉ አቅማቸው በመላው አገሪቱ ተንቀሳቅሰው ከደጋፊዎቻቸው ጋር መገናኘት የሚችሉት እነዚህ ህጎች ሁሉንም የፖለቲካ ሀይሎች በእኩል ማስተናገድ ሲችሉ ብቻ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ህጉ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ገደብ የሚያደርግባቸው ሲሆን : በተግባር የሚታየውም የህጉን ተፈጻሚነትን ነው።

ለዚህ ማሳያ ብዙ ክስተቶችን ማሳየት ይቻላል። በተለይ ከባለፉት ጥቂት አምታት በፓርቲዎች እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩት ጫናዎች በቂ ማሳያዎች ናችው። ሰማያዊ ፓርቲ በአዲስ አበባ : በጎንደር : በአርባ ምንጭ ወዘተ ከተሞች ሰላማዊ ስልፍና ስብሰባዎች ለማድረግና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ለመገናኘት ያደረጉዋቸው ሙከራዎች አንዳንዱን እንዲሰርዙ ሲገደዱ አንዳንዱን ደግሞ በከባድ ጫና አካሂደዋል። የአረና ትግራይ ፓርቲም በልዩ ልዩ የትግራይ ከተሞች ሰላማዊ ስልፍ ለማድረግ ያደረገው ሙከራ ግማሹ ሲስተጓጎል ሌላው ደግሞ በከባድ ተጽእኖ ተካሂዶአል። አንድነት ፓርቲም ያዘጋጃቸው ስብሰባዎች በተመሳሳይ መልኩ ተስተጓጉለዋል። ታድያ ጥያቄ የሚሆነው ከአስር አመት በፊት የነበረው የፖለቲካ ምህዳር ከአሁኑ የሚሻል ከሆነ የዴሞክራሲ ግስጋሴው ወዴት እየተጉዋዘ ነው? ወደ ፊት ወይንስ

እንደ ግመል ሽንት ወደ ሁዋላ? መልሱ እንደ ግመል ሽንት ብሎ ሁሉም የሚስማማበት እንደሚሆን አልጠራጠርም።

በመሆኑም በምርጫ 2007 ህዝብ ቢሳተፍ ወይንም ባይሳተፍ የዴሞክራሲ ሂደቱን አይልውጠውም። ይህ ድምዳሜ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ይመስላል። ለመቀየር ግን አይቻልም ማለት አይደለም። ወያኔ በራሱ ጊዜ ይሻሻላል ማለት ዘበት ነው። ጉዳዩ ያለው በኛው እጅ ነው። ዴሞክራሲን ከምርጫ ጋር ብቻ አያይዞ ማየት ተገቢ አይደለም። በሕብረተሰቡ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን እሴቶች በመገንዘብ በየአምስት አመቱ ከሚደረገው ምርጫ ባሻገር መመልከት ጠቃሚ ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች ከዚህ ቀደም ያደርጉ ከነበረው በበለጠ መልኩ በአላማ ጽናትና በተግባራዊ ስልት ተጠናክረው መውጣት አለባቸው። የጎንዮሽ እንካ ስላንትያን ትተው ፊታቸውን የጋራ ጠላት ወደ ሆነው ወያኔ ማዞር ከምን ጊዜው በላይ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ውጭ አማራጭ ያለ አይመስልም።

# ተጠያቂ ማነው?

**Hiwot Zegeye/ Erlangen**

የኢትዮጵያ መንግስት ፌደራላዊ ስርዓትን የሚከተል ነው። በፌደራላዊ ስርዓት አወቃቀር መሰረት ክልሎች ወይ መንግስታት ይኖራሉ። እነዚህ ክልሎች የየራሳቸው የሆነ ራስ ገዝ አስተዳደር አላቸው። የሁሉም ክልሎች መንግስታት የሚያገናኝ የፌደራል መንግስትም ይኖራል። ፌደራሉ የሁሉም ነው። ክልሎችም ራስ ገዝ ናቸው። ምክንያቱም የፌደራል መንግስት ስልጣንና የክልሎች ስልጣን በሕገመንግስት የተደነገገ ነው። "ሕገመንግስቱ የወረቀት እንጂ የተግባር'ኮ አይደለም" እንበል።

ስለዚህ ሕገመንግስቱን ካልተገበሩ የራሳቸው ችግር ነው። "አሁን ያለው ስርዓት ለይስሙላ እንጂ በትክክል ፌደራላዊ አወቃቀር የለውም" ልንል እንችላለን። ፌደራላዊ ስርዓቱ ለይስሙላ ከሆነ የይስሙላ ስርዓት የመሰረተውን ኢህአዴግ ተጠያቂ ይሆናል የተቃውሞ ሰልፍ ባደረጉ የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የኃይል እርምጃ ተወስዷል። በሰለማዊ ሰዎች ላይ የተፈፀመውን በደል ሐላፊነት መውሰድ ያለበት ማነው? ህወሓት? ኦህዴድ? ብአዴን? ደኢህዴን? ኢህአዴግ ወይስ ተቃዋሚዎች ወይስ ሌሎች የዉጭ ኃይሎች???

እንደ ነ ለተፈፀመው በደል ተጠያቂ ኢህአዴግ ነው ደግሞ , ዜጎች ቅሬታቸውን በሰለማዊ ሰልፍ የመግለፅ ሕገመንግስታዊ መብት አላቸው። ተቃዋሚዎችም የህዝብን ችግር ማጋለጥና ለህዝብ የማድረስ ግዴታ አላቸው። ህዝብማ ተጠያቂ አይሆንም። ምክንያቱም ህዝብ ተጠቂ ነው። ተጠቂነቱን ም እየተቃወመ ነው።

# ፍትህ ያጣ ህዝብ

**Minewar Abdulwahid Kemal/ HOF**

ህወሓት በ1983 ዓ.ም ስልጣን ሲይዝ ልክ ፋሽስታዊው ደርግ ኢትዮጵ ትቅደም ያለምንም ደም በሚል የኢትዮጵያን ህዝብ ልብ ለመግዛት እንደሞከረው ሁሉ በተቆጣጠረው ሚዲያ የደርግን ክፋት አጥብቆ ለፈፈ።ባንፃሩ የህወሓትን ጀግንነትና መልካምነት አጋነው እንዲደሰኩሩ አደረገ።ሁሉንም አይነት የሰብዓዊ መብቶችና የህግ የበላይነትን እናረጋግጣለን ብዙሃኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ነፃ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ በመፍቀድ ነፃ ምርጫ አድርገን ስልጣን እናሸጋግራለን በማለት ለጊዜውም ቢሆን ሁሉንም ፓርቲዎች የሚያሳትፍ የሽግግር መንግስት ተቋቋመ።
ራሱ ወያኔ ጠፍጥፎ የሰራቸውን ፓርቲዎች በማሳተፍ ማለት ነው።ቆየት ብሎም ህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን አቋቋመና ህገ መንግስቱን በሚመቸው መንገድ አፀደቀ።ከዚህ ጊዜ አንስቶ በተለይም መለስና ጓዶቹ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚደፍርና ባህር በር አልባ ለማድረግ ይሰሩ ነበር።በዛን ጊዜ እንደ ኢህአፓ የመሳሰሉ ጠንካራ ፓርቲዎችን ከስርዓቱ ለማግለል የተጠናከረ ስራም ሲሰራ ነበር።ኦነግም ከሽግግሩ መንግስት እንዲወጣ ተደረገ።በቃ የህወሓት አረመኒያዊና አምባገነንነት ከዚህ ጊዜ ወዲህ በጣም እየጎላ መታየት ጀመረ።ሁሉም ነገር እንዳሰቡት አልጋ ባልጋ ሆነላቸው።በቀጥታም ይሁን በድብቅ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሰዶ ማሳደድ ውስጥ አስገቧቸው።ለስልጣን ያበቋቸውን ከ32ሺ በላይ ታጋዮች ሳይቀር ከስራ ያለምንም ድጋፍ አባረሯቸው።እነ ኦነግና ኢህአፓም አሸባሪ የሚል ተርጋ ተለጠፈላቸው።ሁሉም ነገር ለህዝቡ እየከበደ መጣ ቀስ በቀስም የነፃነት ብርሃን እየጠፋ መጣ።ነፃ ፕሬስ ተዘጋ።ለይስሙላ ቢኖር እንጂ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ አድርገን ህዝባዊ መንግስት እንመሰርታለን ያሉት ህልም ሆነ።ነፃ
የተቃዋሚ ፓርቲ እንቅስቃሴ በደህንነቱ እጅ ገባ።የህዝብ የበላይነት በህወሓት የበላይነት ተተካ።አቃቤ ህግና ደህንነቱ ሁሉ ለህወሓት ወያኔ ጠባቂ በመሆን ህዝቡን ማፈን ዋና ተግባሩ ሆነ።ዳኞችም ነፃነታቸው የተጠበቀ አይደለም የህግ ጠበቃዎችም በወያኔዎች በጠላትነት ተፈርጀው ከሙያቸው ስነ ምግባር ውጪ እንዲያገለግሉ በመገደድ ላይ ናቸው።

በአጠቃላይ የመንግስት ሰራተኛ መምህራን ሀኪም ተማሪ ዳኛ ጋዜጠኛ የሃይማኖት አባት ብሎጊስት ሁሉም ማህበረሰብ በአንድ ለአምስት ፖሊሲ ተጠረነፈ።የተለየ አቋም ካለውም በጠላትነት ይፈረጃል። በትምህርት ቤቶች ከ4ኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርስቲ አንድ ለአምስተ አደረጃጀትን በማስፈን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት እየተፈፀሙ ነው።

ህወሓቶች ሁል ጊዜ የሚሮጡት ለሃገር ሳይሆን የግል ፍላጎታቸውን ለሚሟላት ነው።የአገሪቷን አንጡራ ሃብትም እያጋበሱት ናቸው።አቶ ስዩም መስፍን በረከት ስምኦን ስብሃት ነጋ አባይ ፀሓዬ ሃለቃ ፀጋይ አዜብ መስፍን እንዲሁም ሌሎች አጋሮቻቸው ከነቤተሰቦቻቸው በሙስና ተጨማልቀዋል።

የህወሓት አምባገነንነት አሁን የተከሰተ የሚመስላችሁ ትኖራላችሁ ነገር ግን ህወሓት ሲመሰረት ጀምሮ ከነፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪው ነው የተመሰረተው።ልዩነት የሚባል ጨርሶ ድሮም አይቀበልም።ገዢዎቻችን አዲስ ታሪክ እንሰራለን ብላችሁ የሄዳችሁበት መንገድ የሰይጣን መንገድ ስለሆነ መጀመሪያ ከራሳችሁ ጋር ታረቁ።ከዛም ከኢትዮጵያ ህዝብ አናት ላይ እንድትወርዱ የመላው ህዝብ ፍላጎት ነው።የእናንተ እናውቅላችሁዋለን ማለት በገሃድ ታይቶ አሳፋሪ ውጤት ተመዝግቦበታል።ለ23 ዓመታት የከፋ በደል አድርሳችሁብናል።አሁን ግን ይበቃናል።እኛ ለራሳችን የሚበጀንን እንድናደርግ ወቅቱ ግድ ይለናል።ድል ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ!

# የወያኔ መንግስት በኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የሚያደርሰውን ስቃይና ግድያ ያቁም


**Adam Noor Mohammed/Mental**

የወያኔ መንግስት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ጥያቄ እያቀረቡ ያሉ የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪ ዩንቨርሲቲ ተማሪች ላይ የተለመደውን የጭካኔ እርምጃውን

መውሰዱ ይታወቃል ። በርካታ ተማሪዎች በታጠቁ ሃይሎች የጭካኔ እርምጃ ለከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ተዳርገዋል። በተለይም በአንቦ ከተማ ተማሪዎች በግፍ ተገድለዋል። የወያኔ መንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ በተማሪዎች ላይ ተደጋጋሚ የጭካኔ እርምጃዎችን ወስዷል።

በመላ አገሪቷ በወያኔ እርምጃዎች ከተጠቁት ተማሪዎች ውስጥ ግን ትልቁን ግፍ የተቀበሉት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ስለመሆናቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ ሪፖርቶች ይመሰክራሉ። ዛሬ ላለንበት ጠቅላላ አገራዊ ክሽፈት፣ ውርደት እና የመከራ ሕይወት ለከት ያጣው የወያኔ ጭካኔ እና አፈና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ይገኛል።በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ተማሪዎች ላይ፣ በጋዜጠኞች ላይ፣ በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ፤ እንዲሁም በኃይማኖት መሪዎች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና በደል በጋራ ልናወግዘው እና ልንታገለውም ይገባል። በፍትሕ እና በኢ-ፍትሐዊነት፣ በጭቆና እና በነፃነት መካከል ገለልተኛ ሆነው የሚንጠለጠሉበት ገመድ ወይም የሚቆዩበት ደሴት የለም።

ፍትሕ ሲጓደል እያዩ እንዳላዩ መሆን በራሱ ኢ-ፍትሐዊነት ነው። መብት ሲጣስ እያዩ እንዳላዩ መምሰል በራሱ የጣሹ ግራ እጅ መሆን ነው። ንጹሃን ዜጎች በግፍ ሲገደሉ፣ ሲደበደቡ፣ ሲታሰሩ እና በሃሰት ክስ እየተፈረደባቸው በእስር ሲማቅቁ እያዩ ገለልተኛ መሆን አይቻልም። ለፍትህና ለነፃነት በህብረት በመቆም የሰውነትም፤ የዜግነትም ግዴታችንን እንወጣ!




ምስል ከጉግል።

# Democracy is dead in Ethiopia

**Desalegne Abebew and Yalemwork Meswae/Schöneck**

Democracy is a precondition of the flourishing of different values and ways of life. It has been almost 23 years since "democratic government" of TPLF took position of power in Ethiopia. But, Ethiopian people is still thirsty of assets of democracy which are justice, equality, true election, freedom of press and expression, freedom of assembly, access to information and others, that are guaranteed under the nation's Constitution. TPLF government is always the winner in all of the previous elections. The people are not governed by elected politicians, instead by unelected or hated ones. Knowing all these problems, TPLF is not voluntary to solve them with discussion around the table.

For existence of real democracy in Ethiopia, there should be argument, discussion, criticism between the ruling party and the opposition parties. But Ethiopia missed all of these golden elements which are necessary and vital for one democratic population. TPLF does not create opportunities for debating on decisive political problems of the country, on the other hand they act as they solved all of the political problems and as the politics is finished. They do not want to open such stages because of their behavior of being allergic to a question which is a fuel for discussion.

Unfortunately, everything about democracy in Ethiopia remains on the paper. TPLF has gone wrong over the course of democracy. When the people demonstrate or protest for their right, they take antidemocratic measurement on the people. The idea of democratic governance has not flourished in Ethiopia, instead TPLF ironically spark or ignite undemocratic ideas and actions. And they did not know that the road to democracy is often paved by opposite intensions. They are layman and inexperienced for applicability of democracy and they become obstacle for development process of democracy in Ethiopia. As an evidence for the lack of freedom of expression, the TPLF government has arrested six independent bloggers (with a group name of Zone 9) and a journalist. In addition, security forces beat and killed students protesting plan to expand capital boundaries. Ethiopia's heavy handed reaction to the Oromo protests is the latest example of the government's ruthless response to any criticism of its policies. Now it is time for all of us to work together so that Ethiopia will be free from such tyranny and nondemocratic governance.We dream democrat Ethiopia!!!

# Still no freedom of press

**Elsa Hagos/Lahntal**

Prime Minister Meles Zenawi's death in August 2012 and his replacement by Hailemariam Desalegn raised hopes of political and social reforms that would benefit freedom of information. Sadly,

these hopes have been dashed. The repressive anti-terrorism law adopted in 2009 is a threat that continues to hang over journalists, forcing them to censor themselves. Media that dare to violate the code of silence, especially as regards government corruption, are systematically intimidated.

Nine journalists and bloggers are currently detained in Kality prison of Addis Ababa. The regime of EPRDF has accused them as a supporter and mediator of terrorist groups as always. But the reverse is true. The regime is trying to close every holes of criticism. There is no sign of any loosening of the vice that grips the Ethiopian media and the regime is unlikely to tolerate criticism before the elections in 2015. That`s why:- they want to demolish freedom of speech. Down to woyane regime!

# Free religion and government!

**Melese Sebsibe/ HOF**

Because the interferance from Ethiopian regime,As we know Ethiopia is burning by its government. The regime is trying to manage every religious activities through the leadership of the religions.

The country`s constitution is declared that, anybody can follow freely a religion that he like . but practically it is the reverse. So now adays because of the interferance from the regime, religions are under a dictatorial controll of the Woyane/EPRDF regime. This activities of thge regime embarks conflict with in the religious followers between themselves. Muslim ethiopians are a very good example .

Why is the regime of Woyane need to demolished religions?

- Because the followers of every religions are very strong to neglect the mal administration and bad doings of the regime
- Religion has very strong back ground for a country peace, security and unity of the people

- Religion is the backbone of the country. For that matter, Ethiopian government is nowadays blackmailing the younges of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Chruch as a terrorist groups. If you do not beleive the policies of the regime like a Bible ,they give you a terrorist plate number. So, we should have to unite together to avoid this anti-religions regime of woyane. God bless Ethiopia!

# Blue Party in Custody!

**Yoseph Teklu Afewerk/Fulda**

The end of last month, the TPLF lead government has arrested over 30 Semayawi ( Blue) Party members ahead of a protest rally organized by the Party, scheduled to take place in Addis Abeba. The protest rally is being organized fully in compliance with the law.

The police arrested several of the Party's leadership team and several dozen members. The detainees include the party`s Vice-Chairperson, several executive committee members and at least 30 other members have been arrested and being held at several police stations in Addis Ababa. Semayawi Party Chairperson, Eng. Yilkal Getnet was also detained but has been released soon after he was taken to the Police station.

Blue Party is largely a political organization of the youth, who are characterized as non-violent, law abiding and yet defiant to fight the tyrannical EPRDF regime to the end. The detention is a very good example of the manner of dictatorial regime of EPRDF. Long live to Blue party!

# Arresting Journalists continued!

**Murad Awel/Fulda**

In Ethiopia the EPRDF regime continues to clamp down dissent and journalists. In a latest repressive act on journalist and bloggersthe

dictatorial regime last month arrested zone 9 bloggers Abel Wabella,Atnaf Berhane (translator for global voices), Befkadu Z.Hailu,Mahlet Fantahun,Natnail Feleke alon with Journalist Tesfalem Woldeyes.

The imprisonment of Eskinder Nega, Reeyot Alemu, Wunshet Taye among other Journalists, several opposition members and supporters on trumped up charges raised serious concern from international rights organizations. Several reports of US state department , statement by higher representative Cathrine Ashton of EU external action service raised concern regrading``lack of clarity`` on Ethiopia`s vaguely defined Anti-Terrorism proclamation –used to crack down dissent. The UK gov`t also recently issued a report expressing its concern on human right abuses in Ethiopia saying``the UK is concerened about continuing restrictions on opposition and dissent in Ethiopia, through use of the Anti-Terrorism Proclamation(ATP) and the Charities and Societies Proclamation(CSP)``.

The international community can and should do more to secure the relese of innocent political prisoners in Ethiopia which requires concreate and coordinated action. Long live to Ethiopia!

# The need for democracy is a crime

**Dawit Tadele / Groβ gerau**

The current one party government of Ethiopian people's revolutionary democratic front (EPRDF) is controlled by an elite group from ethnic based TPLF in power for over 22 years .almost in every aspect of life in the country the regime failed to fulfill its duty as the protector and benefit provider to its people as it should have been . Life has always been difficult, but conditions are worsening for many, not only in regards to freedom and opportunity. In general there is no freedom of low and accountability, no independent judiciary system, no independent institutions, no free press and media and no fair and free election.

Oppressive government of Ethiopia continuously deteriorating lives of its citizens from day to day the country has become a battle ground of pain and sufferings for it's citizens under the suppressive immoral dictatorial ruling system .now a days in Ethiopia continues detention, torture and smother has become the main duty of the TPLF regime especially for journalist, bloggers political activists.

The regime proclaimed ant-terror law to avoid a peaceful dissent writing and speaking about the need for democracy and human rights according to the low anyone who stands for its rights are a terrorist ,a journalist who exposes what really going on a terrorist ,an opposition party members are a terrorist, and anyone who support or even challenges TPLF is a terrorist .In general writing and speaking about the need of democracy and human right in Ethiopia is a crime .this is the tactic of TPLF to shifting the public attention away to other issues by arrest and sentenced journalist and bloggers as a terrorist. All Ethiopians know TPLF drama. I have no doubt that victory and success will be the people of Ethiopia we should avoid the dictatorial regime by all kinds of struggle. In the near feature this being true. Free all journalist bloggers and political activists.
«God bless Ethiopia »

**FREE PRESS!**